የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES'REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ6 ዓመት የሥራ ቆይታ ወቅት የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ያጋጠሙ ችግሮችን አስመልክቶ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት


**ዝግጅት**

በወ/ሮ ሒሩት እምቢአለ

በአቶ ፒተርዘግሬት ለይኩን

በአቶ ጌታቸው ሎሻሞ


ሰኔ 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ


ምስጋና ..... 4

ምህፃረ ቃላት ..... 5

ምዕራፍ አንድ ..... 6

1.1. መግቢያ ..... 6

1.2. ጥናቱ ይዟቸው የተነሳቸው ችግሮች ..... 7

1.3. የጥናቱ ዓላማ ..... 8

1.3.1. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 8

1.4. የጥናቱ ወሰን ..... 8

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 9

1.6. የጥናቱ ውስንነት ..... 9

ምዕራፍ ሁለት ..... 10

2. የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ ..... 10

2.1. የሕግ አወጣጥ ተግባርን አስመልክቶ ..... 10

2.2. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ..... 11

2.2.1. ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች ..... 12

2.2.2. ቼክ ሊስትን በተመለከተ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች ..... 13

2.3. የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ዕቅዶች በመገምገም ሂደት ትኩረት የተረጉባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ..... 13

2.4. የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን የዕቅድ አፈፃፀም ሲገመገም ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ..... 14

2.5. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ክንውንን በሚመለከት ..... 15

2.6. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች በተመለከተ ..... 16

2.7. የአቅም ግንባታ ተግባራት አፈፃፀም ..... 17

2.8. የመስክ ምልከታ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች ..... 17

2.9. የመራጭ ህዝብ ውክልና ሥራን በተመለከተ ..... 18

2.10. የዲፕሎማሲ ሥራን በተመለከተ ..... 18

ምዕራፍ ሦስት ..... 20

3. የጥናቱ ዜዴ (Research method) ..... 20

3.1. የአጠናን ዘዴ (Method) ..... 20

3.2. ጥናቱ የተከናወነበት ቦታ (Study area) ..... 20
3.3. የመረጃዎች ዓይነትና ምንጭ (Data type and source) ..... 20
3.4 የአጠናን ስልት ..... 21
3.5 የናሙና አወሳሰድና የናሙና መጠን (Sampling techniques and size) ..... 21
3.6. የመረጃ ትንተና እና አቀራረብ ስርዓት (Data analysis and presentation) ..... 22
ምዕራፍ አራት ..... 23
4. የጥናት ውጤቶችና መረጃ ትንተና /Research result and Discussion/ ..... 23
4.1. ምክር ቤቱ በ5ኛው ዙር በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው ሥራዎችን ሲያከናውንበት የነበረው አጠቃላይ የሥራ ሂደትን በተመለከተ ..... 23
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 23
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 25
4.2. በምክር ቤቱ በተሠሩ ሥራዎች ዙሪያ የነበሩ ጥንካሬዎችና እጥረቶችን በተመለከተ ..... 27
4.2.1. የሕግ ማውጣት ሥራን በተመለከተ ..... 27
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 27
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 28
4.2.2. የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ የታዩ ጥንካሬዎችና እጥረቶች ..... 29
4.2.2.1. የተቋማትን ዕቅድና የዕቅድ የአፈፃፀም ሪፖርት ሥራን በሚመለከት ..... 29
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 29
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 31
4.2.2.2. የመስክ ሥራዎችን በሚመለከት ..... 32
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 32
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 33
4.2.3. የዲፕሎማሲ ሥራን አስመልክቶ ..... 34
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 34
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 34
4.2.4. የውክልና ሥራን በተመለከተ ..... 35
ሀ. በጥንካሬ የታዩ ..... 35
ለ. በእጥረት የታዩ ..... 36
5. ማጠቃለያና ምክረ ሐሳቦች/Conclusions and Recommendations/ ..... 38

5.1. ማጠቃለያ/ Conclusions/ ..... 38

5.1.1. ሕግ አወጣጥን በተመለከተ ..... 38

5.1.2. ክትትልና ቁጥጥር ተግባርን አስመልክቶ ..... 39

5.1.3. የህዝብ ውክልና ሥራን በሚመለከት ..... 39

5.1.4. የዲፕሎማሲን ሥራን በተመለከተ ..... 39

5.2. ምክረ ሐሳቦች / Recommendations/ ..... 40

**5.2.1. በቀጣይ ጊዜ የነበሩ ችግሮችን ለማስወገድ ምክር ቤቱ ሊሠራቸው የሚገቡ ጉዳዮች** 40

5.2.2. **ቋሚ ኮሚቴዎችን አስመልክቶ** ..... 42

**5.2.3. በቀጣይ ጊዜ የነበሩ ችግሮችን ለማስወገድ የም/ቤቱ ጽ/ቤት** ..... 42

ዋቢ መፅሀፍት (References) ..... 44

የቃል መጠይቅ ..... 45

# ምስጋና

ይህ የዳሰሰ ጥናት እንድናከናውን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የሙያዊ ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ፤ የተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ሙያዊ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ስላቀረበልን የሥራ ጥሪ ምስጋናችን የላቀ ነው፡፡

በመቀጠል ሥራውን በበላይነት ሲያስተባብሩ የነበሩትን ዶ/ር ሄኖክ ስዩም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የሙያዊ ድጋፍ አገልግሎት ዘርፍ ም/ዋና ፀሐፊ፣ አቶ አስማረ ካሳሁን የተቋማት ክትትልና ቁጥጥር ሙያዊ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር እንዲሁም አቶ በላይ ለገሰ የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በእኛ ላይ ስለነበራቸው እምነት ከልብ እናመሰግናለን፡፡

# ምህፃረ ቃላት

ጽ/ቤት----------------------------ፅሕፈት ቤት

ም/ዋና----------------------------ምክትል ዋና

ዓ.ም-------------------------------ዓመተ ምህረት

ም/ቤት----------------------------ምክር ቤት

መ/ቤቶች-------------------------መሥሪያ ቤቶች

ዕትዕ -----------------------------ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. መግቢያ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሕግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ አካላትን መከታተልና መቆጣጠር፣ የመራጮች ውክልና እና የዲፕሎማሲ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ ምክር ቤቱ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የምክር ቤቱን የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 በተሻሻለው መሠረት የራሱን አደረጃጀት በመቅረጽ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን በዚህም አማካሪ ምክር ቤት፣ ቋሚ ኮሚቴዎች እና ንዑሳን ኮሚቴዎች እና አስተባባሪ ምክር ቤት አደረጃጀቶችን በመጠቀምና የመከታተያ ቼክ ሊስቶችን በማዘጋጀት፣ የመስክ ምልከታ በማድረግ፣ ከአስፈፃሚ አካላት ጋር የጋራ ውይይቶችና ምክክሮችን በማደረግ የሥራ አፈፃፀማቸውን ጥንካሬዎችና እጥረቶችን ይለያል፡፡ የቋሚ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ቋሚ ኮሚቴዎች በጋራና በተናጠል በሚያደርጓቸው መደበኛ ስብሰባዎች የአስፈፃሚ አካላትን ዕቅዶችና ይህን ተከትለው የሚቀርቡ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጣሉ፡፡ እነዚህን ግምገማዎች መሠረት በማድረግ ከሚሰጡ አስተያየቶችና የጋራ ስምምነቶች ባሻገር የጎላ የአፈፃፀም ክፍተት ያለባቸው መሥሪያ ቤቶች የእርምትና የማስተካከያ ተግባራትን እንዲወስዱ የጽሁፍ ግብረ መልሶችን እንዲሁም አስፈፃሚ መ/ቤቶችን በአካል በመጥራት ሥራቸውን እያቀረቡ ግብረ መልሶችን ሲሰጧቸው መቆየታቸው ይታወቃል፡፡

ሕግ በማውጣት ሂደት ምክር ቤቱ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት በኩል የተላኩለትን ሕጎች በተመለከለተ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በዝርዝር እንዲታዩ በማድረግ ተገቢውን ሂደት አልፈው እንዲመጡና ለምክር ቤቱ ቀርበው እንዲፀድቁ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የሕዝብ ውክልና ሥራን በተመለከተ አባላቱ በዓመት ሁለት ጊዜ ወደ ምርጫ ክልላቸው እንዲሄዱና ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር እንዲወያዩና በውይይታቸው ወቅት የሚነሱ ጥያቄዎችን ምክር ቤቱ በተደራጀ አግባብ የሚመለከታቸው የመንግሥት አስፈፃሚ መ/ቤቶች ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡበት የማድረግ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በተመለከተ በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ 6/2008 እንደተሻሻለው ዲፕሎማሲን በተመለከተ የወዳጅነት ቡድኖችን በማቋቋም ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡

ይህም ጥናት ቋሚ ኮሚቴዎች ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በሚፈፅሙበት ወቅት የነበራቸው ጥንካሬዎች፣ እንዲሁም የነበሩ እጥረቶች እና ለወደፊት መስተካከል ያለባቸውን ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት በቀጣይ በሕዝብ ተወክሎ ለሚመጣው ፓርላማ ምቹ የሥራ ሁኔታን ለመፍጠር የተዘጋጀ የዳሰሳ ጥናት ውጤት ነው፡፡

በዚህ ጥናት የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ፣ ጥናቱ ይዟቸው የተነሳቸውን ችግሮችን፣ የጥናቱን አጠቃላይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የአጠናን ዘዴ(ስልት)፣ በክፍል አንድ የቀረቡ ሲሆን፤ በክፍል ሁለት አንዳንድ ርእሰ ጉዳዩን የተመለከቱ ሰነዶች ተዳሰዋል፣ በክፍል ሦስት የጥናቱ ዘዴዎች ተካተዋል፡ በክፍል አራት የጥናቱን ውጤቶችና ትንተና እንዲሁም በክፍል አምስት ማጠቃለያ እና ምክረ ሐሳቦችን በማካተት ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. ጥናቱ ይዟቸው የተነሳቸው ችግሮች

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች የተለያዩ ሕጎችን በማውጣት፣ የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ዕቅዶችና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን በመገምገም፣ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ያሉበት ድረስ በአካል በመገኘት የመስክ ምልከታን በማድረግ ለአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን የማስተካከያ እርምቶችን እንዲወስዱ አስተያየቶችን እና ግብረ መልሶችን በመስጠት፣ የመረጣቸውን ህዝብ በመወከል የሚተገበሩ ሥራዎችን አስመልክቶ የሕዝብ ጥያቄዎችን የመሰብሰብና ምላሽ እንዲሰጣቸው የማድረግ እና የዲፕሎማሲ ሥራን በመሥራት ሂደት የምክር ቤቱ 5ኛ ዙር የሥራ ዘመን ባለፉት 6 ዓመታት ሥራዎችን በሚያከናውንበት ወቅት ከአሠራርና ከአተገባበር አንፃር የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለአብነትም፡- ሕግ በሚወጣበትና በሚገመገምበት ወቅት ያሉ እንቅፋቶች እንዲሁም ከክትትልና ቁጥጥር ተግባራት ጋር ተያይዞ ለአስፈጻሚ አካላት ከሚሰጡ ግብረ መልሶችና ፋይዳቸው አንፃር በአባላት በተለያዩ መድረኮች የሚነሱ አስተያቶችና ቅሬታዎች ለመጥቀስ ይቻላል፡፡ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች በዕቅዳቸውና በዕቅድ አፈፃፀማቸው ላይ የተሰጣቸውን ግብረ መልስ በተመለከተ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰዳቸውን በማረጋገጥ በኩል የክትትልና ቁጥጥር ጉድለት መኖሩ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር በኦዲት ያገኛቸውን ግኝቶችን በማስተካከልና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ በኩል የጎላ ለውጥ አለመምጣቱ፣ በምክር ቤቱ ለአስፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት የታወቀ የጊዜ ገደብ የሌላቸው መሆኑ፣ የተጠሪ ተቋማትን ሪፖርት ለክትትልና

ቁጥጥር ተግባር በግብዓትነት አለመጠቀም፣ ለክትትልና ቁጥጥር የሚውሉ ወጥ የሆኑ ስታንዳርዶችና /standard/ ቼክ ሊስቶች አለመኖር፣ የወጡ ሕጎችና ደንቦች ምን ያክል ተፈጻሚ አንደሆኑ ትኩረት ሰጥቶ አለመከታተል እና የተሻለ አፈፃፀም ላሳዩ አስፈፃሚ አካላት የማበረታቻ ስልት አለመኖር ሲሆኑ ይህም ምክር ቤቱ ተግባራቱን ሲያከናውን በነበረበት ወቅት አሠራሩ ወጣ ገባ መሆኑ፡፡

ከዚህም በመነሳት ቀጣይ ለሚመጣው ፓርላማ እነዚህን ችግሮች በመለየት ሥራዎችን በተሻለና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሥራት ያስችለው ዘንድ ምክር ቤቱ 5ኛ ዙር የሥራ ዘመን ባለፉት 6 ዓመታት ሥራዎችን በሚያከናውንበት ወቅት የነበሩ ጥንካሬዎች፣ እጥረቶች እና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በጥናት በመለየት የተሻለ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማስቻል ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር የሥራ ዘመን በ6 ዓመት የሥራ ጊዜ ቆይታው አጠቃላይ ሥራዎችን ሲያከናውንበት የነበረውን የአሠራር ሂደት ማጥናትና በቀጣይ ተመርጦ ለሚመጣው ምክር ቤት የተሰጠውን ተልዕኮና ኃላፊነት በላቀ ደረጃ ለመወጣት የሚያስችለውን አሠራር ማመላከት ነው፡፡

### 1.3.1. ዝርዝር ዓላማዎች

- ✓ ምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው ሥራዎችን ሲያከናውንበት የነበረውን ሂደት ማጥናት፣
- ✓ በምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው የነበሩ ጥንካሬዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን መለየት፣
- ✓ በምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር በ6 ዓመት የሥራ ቆይታ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና በቀጣይ ተመርጦ ለሚመጣው ምክር ቤት ለይቶ ማስቀመጥ፣

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር የሥራ ዘመን በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው ወቅት ቋሚ ኮሚቴዎች ያከናወኗቸው ተግባራት ሕግ በማውጣት፤ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን የመከታተልን የመቆጣጠር ሥራ፣ የዲፕሎማሲ ሥራዎች እንዲሁም የውክልና ሥራዎችን

ሲያከናውኑ በነበሩበት ጊዜ የነበሩ የአፈፃፀም ሂደቶችና በሂደቶቹም የታዩ ጥንካሬዎችና እጥረቶች በመለየት በቀጣይ ለሚመጡ የምክ ቤት አባላት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው የሚያስችል ምክረ ሀሳብ ለማቅረብ እና የምክር ቤቱ ጽ/ቤት እንዲሁም በምክር ቤቱ በሚገኙ በ10ሩ ቋሚ ኮሚቴዎች የተወሰነ ነው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ምክር ቤቱ በ5ኛ ዙር የሥራ ዘመን በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመውሰድ በቀጣይ ተመርጦ ለሚመጣው ምክር ቤት ሥራዎችን በተሻለ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል አሠራር በመዘርጋትና በምክር ቤቱ አባላት ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት ብሎም ቀጣይ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ለተዛመደ ጥናት እንደ መነሻ ወይም ግብዓት ሆኖ እንዲያገለግል የሚያስችል ይሆናል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት በአግባቡ የተሰበሰበና የተደራጀ ዶክመንቶች አለመኖር እንዲሁም ጥናቱ የሚያካትተው ምክር ቤቱንና በምክር ቤቱ ያሉ ቋሚ ኮሚቴዎችን ብቻ በመሆኑ ጥናቱ በምክር ቤቱ ተግባራትና ኃላፊነትን ብቻ የሚዳስስ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ጽሁፎች ዳሰሳ

### 2.1. የሕግ አወጣጥ ተግባርን አስመልክቶ

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 መሠረት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት ከሆኑት መካከል ሕግ ማውጣት አንዱ ነው፡፡ ይህ ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኮ በተለይም አዲስ ሕግ ማውጣት፣ ነባር ሕግ ማሻሻል ወይም መሻር፣ የዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ማጽደቅና ውሳኔዎችን ማስተላለፍ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ለፌዴራል መንግሥት በተሰጠው ሥልጣን ክልል ውስጥ የሆኑ ዝርዝር ሕጐችን በማውጣት ተግባራዊ ሲደርግ ቆይቷም፡፡ ሥራ ላይ የዋሉ ሕጎችን በሚመለከት ምክር ቤቱ በ5ኛው የሥራ ዘመኑ ባለፉት 6 ዓመታት በቁጥር ከ310 በላይ የሚሆኑ ዓዋጆችን ከማፅደቁም ባሻገር የተለያዩ ውሳኔዎች አሳልፏል፡፡ በምክር ቤቱ 5ኛው የሥራ ዘመን ለምክር ቤቱ የተላኩ ረቂቅ ሕጎችን ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በዝርዝር እንዲታዩ ተደርጓል፡፡[1] በዚህም ቋሚ ኮሚቴዎች የተመራላቸውን ረቂቅ ሕጎችን በንባብ በመስማት ውይይት የሚደረግባቸው ሲሆን ከውይይታቸው በመነሳት አስፈላጊ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት የሚመለከታቸውን አስረጂዎች በመጥራት በረቂቅ ሕጉ ላይ ውይይት ይደረግበታል፡፡ በአስረጂ መድረኮች ላይ የተገኙ ምላሾችና ማስተካከያዎችን እንደ ግብዓት በመውሰድ ለቀጣይ የሕዝብ ይፋ ውይይት እንዲደረግበት በመገናኛ ብዙሃን ሕዝብ እንዲሳተፍበት ጥሪ ተደርጎ ከሕዝብና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በረቂቅ ሕጉ ላይ ውይይት በማድረግ የተገኙ ግብዓቶችን በመውሰድ ቋሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር እይታ በማድረግ በረቂቅ ሕጎቹ ላይ እንዲካከቱ ወይንም እንዲቀነሱ የሚስፈልጉ አንቀፆችን፣ ዐረፍተ ነገሮችንና ቃላቶችን በመለየት ዝርዝር ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ቀርበው እንዲጸድቁ ተደርገዋል፡፡ እነዚህ ጸድቀው የወጡ ሕጎች በሃገር ደረጃ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የጎላ አስተዋጽዖ እያደረጉ ያሉ ናቸው፡፡

---

[1] *በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የ 5 ዓመት መሪ ዕቅድ ገጽ 9*

## 2.2. የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት የሚያከናነው ተግባራትን ለመፈፀም በደራጃቸው ቋሚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ሲሆን እነዚህም ቋሚ ኮሚቴዎች የመንግሥትን ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፣ የወጡ ሕጐችን፣ የታቀዱ የረጅም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችና ለዕቅዶዶቹ የተመደበ በጀት በዕቅዳቸው መሠረት ተግባራዊ መደረጉን፣ የህዝቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥን በተመለከተ ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን ውጤታማ ለማድረግ ምክር ቤቱ  የተለያዩ ስልቶችን ይከተላል፡፡ በዚህ መሠረት በፌዴራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን እና በአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች መካከል የተቀናጀ አሠራር መኖሩን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች በሥራ ዘመናቸው ለማሳካት ያቀዷቸውን ዓላማ፣ ግቦች፣ ውጤቶች እንዴት እንደሚለኩ፣ በማን እንደሚለኩ እና መቼ እንደሚለኩ በግልጽ የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም ከዕቅዳቸው የሚጠበቁ ውጤቶችን ከስትራቴጂ ግቦች እና ከቁልፍ ተግባራቶች ጋር እንዴት እንደሚተሳሰሩ፣ የአፈፃፀም መረጃዎች እንዴት እንደሚሰበሰቡ፣ እንደሚተነተኑ እና ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም አስፈላጊ ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ ለማሟላት ከማገዙም በላይ ከአፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለህዝብ ጠንካራ የሆነ የግልጽነትና የተጠያቂነት ሥርዓትን ለመተግበር ያስችላል፡፡ የክትትል እና የቁጥጥር ስራዎች በዕቅድ ታቅደው የሚፈፀሙ ሲሆኑ በዚህም፡-

- በዕቅድ የተያዙ ዓላማዎችንና ግቦችን መለየት
- የክትትልና ቁጥጥር ቼክ ሊስቶችን፣ አመላካቾችንና አዋጭነታቸውን መወሰን
- የክትትልና ግምገማ ዘዴዎችን መወሰን፣
- የአፈፃፀም ሁኔታዎችን ማስቀመጥ በማን እንደሚካሄድ፣  አሁናዊ  ውጤቶችና  ያለፉ ጊዜያት ግኝቶችን እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ መወሰን፣
- ውስጣዊና ውጫዊ የክትትል፣ቁጥጥና ግምገማ ሀብትና አቅምን መለየት
- የክትትል እና የቁጥጥር ድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት
- በአዎንታዊነት የሚገለጹ የክትትል እና የቁጥጥር ግኝቶች የሚስፋፉበትና ጥቅም ላይ የሚውሉበት ስትራቴጂ መንደፍ፣

### 2.2.1. ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀምን በተመለከተ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች

በም/ቤቱ መሪ ዕቅድ ላይ የተቀመጡ የአቅም ግንባታ፣ ክትትልና ቁጥጥር፣ ሕግ አወጣጥ፣ ሙያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት እንዲሁም ሌሎች ከህዝብ ተሳትፎ፣ የዴሞክራሲ ተቋማት ግንኙነት ሁኔታዊ ግምገማ ላይ የተቀመጡ ጉዳዮች ሁኔታዊ ግምገማ እንደ መነሻ መውሰዳቸው፣ የምክር ቤቱ ዕቅድ ላይ የተቀመጡ ቁልፍ ችግር፣ ቁልፍ ተግባር፣ ዓላማዎች፣ ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት የም/ቤቱን ተልዕኮ እንደሚያስፈፅም አንድ አካል ከዕቅዳቸው ጋር ተልዕኮዎችን በተጣጣመ መልኩ መነሻ መደረጋቸው፣ ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ ለመልካም አስተዳደርና ሰላም መስፈን፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት መረጋገጥ የሚረዱ ሕጎችን ማውጣት፣ በምክር ቤቱ ለወጡ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች ማስፈፀሚያ የተመደበ ሃብት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ መዋሉን በመከታተልና በመቆጣጠር የሕዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ የምክር ቤቱ የመድብለ ፓርቲ ፓርላሜንታዊ ዲሞክራሲ የሚጐለብትበትን አሠራርና ሥርዓት መዘርጋት፣ በምክር ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ፍትሐዊና ሚዛናዊ የሆነ ተሣትፎ መኖሩን ማረጋገጥ፣ የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታን እንደ መነሻ መገምገማቸውን ተለይተው በዕቅዱ እንዲካተቱ መደረጉ እና ቁልፍ ችግሮችን በመለየትና በመተንተን የዕቅዱ አካል መደረጋቸው፣ የምክር ቤቱን መሪ ዕቅድ መነሻ በማድረግ ቋሚ ኮሚቴዎች ዕቅዳቸውን ማዘጋጀታቸው፣ የክትትልና ድጋፍ ቼክሊስት በማዘጋጀት የጋራ አስተሳሰብ እንዲያዝበት በቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የጋራ የማድረግ ተግባር መኖሩ፣ የክትትልና ቁጥጥር ቼክሊስትና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ላይ ለቋሚ ኮሚቴው አመራር እንዲሁም አባላት በማቅረብ (ኦሬንቴሽን በመስጠት) የሚቀርቡ ማስተካከያዎችን በመቀበል የሥራ መመሪያ በማድረግ ለመሥራት አቅጣጫ መወሰዱ፣ የመስክ ምልከታ እቅድና የተቋማት የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀትና በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ የጋራ መግባባት በመፍጠር ጸድቆ ወደ ሥራ እንዲገባ መደረጉ፣ ሥራዎችን በግቦች በመለየት ማስቀመጣቸውና በእያንዳንዱ ግብ ሥር ተግባራቶች ተለይተውና ተዘርዝረው መቀመጣቸው፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች ከተግባር ተነጥሎ በራሱ የሚቆም ስለማይሆን በእያንዳንዱ ተግባሮቻቸው ውስጥ ማለትም ከአስፈፃሚ የመንግሥት አካላት በመድረክ በሚደረጉ ግምገማዎችና ውይይቶች፣ በረቂቅ ሕግ ምርመራ ሂደት፣ ኮሚቴው በሚያደርገው የዕቅድ እና የሪፖርቶች ግምገማ ውይይቶች መልሶ የአባላትን አቅም ሊገነባ በሚያስችል መልኩ መጠቀም፣ በተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት በሚዘጋጁ የተለያዩ ስልጠናዎች፣ ሴሚናሮች ፣ አውደ ጥናቶችና የምክር መድኮች ላይ አባላት እንዲሳተፉ ጥሪ ሲቀርብ አስፈላጊነቱ ከተልዕኮአቸው አንፃር

እየተመዘነ እንዲሳተፉ ለማድግ ግብ ማስቀጥ መቻላቸው፣ አስፈላጊነታቸው በታመነባቸው ርዕሰ ጉዳዮች በቋሚ ኮሚቴዎች ደረጃ በየራሳቸው ለስራዎቻቸው ውጤታማነት የጎላ ፋይዳ ያላቸውን ርዕሰ ጉዳዮች በመምረጥ ግንዛቤውና ዕውቀቱ ያላቸው አባላት እና ባለሙያዎች ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት አድርገው ለመሥራት በዕቅድ መካተታቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

### 2.2.2. ቼክ ሊስትን በተመለከተ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን የበጀት ዓመት መሪ ዕቅድን እንደ መነሻ በመውሰድ፣ የቋሚ ኮሚቴዎች ያለፈውን የበጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን እንደ መነሻ መውሰድ መቻላቸው፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን እንደ መነሻ መውሰዳቸው፣ የክትትልና ቁጥጥርና ድጋፍ ተግባራትን እንደ መነሻ መውሰዳቸው፣ የሕግ አወጣጥ ተግባራትን እንደ መነሻ መወሰዱ፣ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የተሰሩ ሴክተር ዘለል ተግባራትን እንደ አንድ የሥራ አካል አድርጎ እንደ መነሻ መውሰዳቸው እና የዕቅድ አፈፃፀም ጥንካሬዎች፣ እጥረቶች፣ መልካም አጋጣሚዎች እና ሥጋቶችን እንደ መነሻ መውሰድ መቻላቸው ዋና ዋና መሠረታዊ ትኩረቶች ናቸው፡፡

## 2.3. የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ዕቅዶች በመገምገም ሂደት ትኩረት የተረጉባቸው ዋና ዋና ነጥቦች

የዕቅዳቸውን የሁኔታ ግምገማ፣ የአመራር፣ የፈፃሚ፣ የባለድርሻ አካላት ሚና በጥንካሬና በእጥረት፣ የነበሩ ማነቆዎችና መፍትሔዎቻቸው፣ ቁልፍ ችግሮች እና ተግባራት፣ ግልፅ ግቦች የተቀመጠና የ2ኛውን ዕትዕ /ስትራቴጂ ዕቅድ/ ግቦችን ለማሳካትና ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተጣጣመና የተገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የሚያሠራ አደረጃጀት፣ የሰው ሀይልና በጀት መመደቡን ማረጋገጥ፡፡ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ዕቅዳቸውን ሲያቅዱ የመነሻ ሁኔታዎችንና የሥራ አካባቢውን በሚገባ ተገምግሞና ተተንትኖ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋጥ፡፡ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ምክር ቤቱ ያጸደቀላቸውን የመደበኛና የፕሮግራም በጀቶችን የሚገልጽ የድጊት መርሃ ግብር በየሩብ ዓመቱና በየዘርፉ ተከፋፍሎ ለክትልና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ መዘርዘሩን ማረጋገጥ፡፡ የአስፈፀሚ መ/ቤቶቹንና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ሀብትና ንብረት ከኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት በፀዳ መልኩ ለመተግበር የሚያግዙ ግልፅ አሠራሮችን ተለይተው

መቀመጣቸውን ማረጋገጥ፣ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶቹ ዕቅዳቸው ባለድርሻ አካላትን የለየና የግንኙነት አግባብን ያስቀመጠ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በአፈፃፀም ላይ ለሚፈጠሩ ክፍተቶች/ችግሮች/ ለመለየትና ለመቀበል እንዲሁም አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የተለዩ ምቹ ሁኔታዎችና የአሰራሮች ሥርዓቶች መኖራቸውን እና ፈጣን መፍትሄ ለማስቀመጥ የሚያግዝ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመርና ለማስፋት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዕቅድ ክለሳ ለማድረግና ፈጣን ምላሽ /ግብረ መልስ/ ለመስጠት የሚያስችል አሠራር መኖሩን ማረጋገጥ፣ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማቶች የበጀት አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ከብልሹ አሠራር የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣ ከምክር ቤቱ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላቶች የሚሰጣቸውን ግብረ መልሶች፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችን እና ለሚነሱ ህዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች /የሴቶች ጉዳይ፣ HIV/Aids፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች፣ የአካል ጉዳተኞች እንደየ ሥራ ባህሪያቸው ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ አሠራሮች በዕቅዳቸው መካተታቸውን ማረጋጥ፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አግባብ የዕቅዳቸው አካል መደረጉንና ለዚህም ማስፀሚያ የሚሆን አደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ በዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ወቅት የሚታዩ ዋና ዋና ተግባራቶች ናቸው፡፡

## 2.4. የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን የዕቅድ አፈፃፀም ሲገመገም ትኩረት የሚደረግባቸው ዋና ዋና ነጥቦች

የሚቀርቡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ከታቀደው ስትራቴጂ ዕቅድ፣ ከዓመቱ ዕቅድ፣ ከተጣሉ ግቦችና ተግባራት ጋር ተነፃፅረው የደረሱበትን የአፈፃፀም ደረጃ በግልፅ በሚያመላክት አግባብ የቀረቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ በቀጣይ ሊኖሩ በሚችሉ የለውጥና ሪፎርም ስራዎች ጋር በተያያዘ በጥናት የተዘጋጁና የታቀዱ አሠራሮች ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋጥ፣ የመሥሪያ ቤቶቹንና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ሀብትና ንብረት ከኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት በፀዳ መልኩ ለመተግበር የሚያግዝ ግልፅ አሰራሮችን ለይቶ መታቀዱንና አፈፃፀሙም በሪፖርታቸው በንጽጽር መቅረቡን ማረጋገጥ፣ በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት ግኝቶችና የተሠጡ አስተያየቶችን ተከትሎ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና በወቅቱ ለዋና ኦዲተር ሪፖርቱ መላኩን ማረጋገጥ፡ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የታቀዱ

ዕቅዶችን ለማሳካት እና ዘላቂ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ የሚያስችል እና የህግ ማዕቀፍ ክፍተቶችን መሙላት፣ ደንብና መመሪያ ያልወጣላቸው እንዲወጣላቸው በማድረግ ተፈጻሚነታቸውንና የአስፈፃሚ አካላት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑን ማረጋጥ፣ የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ተጠያቂነትን ማስፈን በሚቻል ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፣

ዘርፈ ብዙ ሥራዎች /የሴቶች ጉዳይ፣ HIV/Aids፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች፣ የአካል ጉዳተኞች እንደየሥራ ባህሪያቸው ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ ግልፅ ዕቅድ መታቀዱንና አፈፃፀሙም በሚቀርቡ ሪፖርቶች ውስጥ በንጽጽር መቅረቡ ይረጋገጣል፣ ለተሰጡ ግብረ መልሶች ተፈፃሚነታቸው የማረጋገጥ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

## 2.5. የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ክንውንን በሚመለከት

ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች በሚከታተሏቸው ተቋማት የመልካም አስተዳደር የንቅናቄ ማቀጣጠያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በተደራጀ የልማት ሰራዊት እየታገዘ የህዝብን ጥያቄ ሊፈታ እና ተጠቃሚነትን ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ መከናወኑን በበቂ ሁኔታ ክትትል ቁጥጥር ለማድረግ እና በሁሉም ቋሚ ኮሚቴም ውስጥ መልካም አሰተዳደርን ማስፈን፣

**ይህንንም ሥራ ተፈፃሚ ለማድረግ ያስችል ዘንድ፡-**

- ሁሉም ተቋማት የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሥራዎች ተግባራዊ መሆናቸውን መገምገም፣
- በሁሉም ተቋማት የሲ/ሰ/የለውጥ መሳሪዎች በተቋማት የዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቀሴ ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ ማቀጣጠያ እቅዱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እና መፍትሔዎች ለይቶ ያስቀመጠና ተግባር ላይም የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የዜጎች ቻርተር መዘጋጀቱና ከህዝብ (መንግሥት) ክንፎች ጋር የጋራ መሆኑን ማረጋገጥ፣
- በተቋማት የወጡ አዋጆች ደንብና መመሪያ የተዘጋጀላቸው መሆናቸውንና ተደረሽነታቸውን ማረጋገጥ፣

- ቋሚ ኮሚቴዎች በሚሰሯቸው ማንኛውም ስራ በተለይም በስልጠና፣ በመስክ ጉዞ እንዲሁም አልፎ አልፎም ቢሆን የውጭ ጉዞ በቋሚ ኮሚቴዎቹ የሚደረግ ከሆነ በአሳታፊነትና በግልጽነት ተግባራዊ ማድረግ፣

## 2.6. የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች በተመለከተ

በምክር ቤቱ ሥራዎች ውስጥ ተካትተዉና በሀገር ዓቀፍ ደረጃ አቅጣጫ ተቀምጦላቸዉ መፈጸም ከሚገባቸው ሥራዎች መካከል የባለብዙ ዘርፍ ተብለዉ የተለዩ ማለትም የሴቶችና ሕፃናት፣ የወጣቶች፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና የአካባቢ ጥበቃንና ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስን የሚመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮችን በማካተት ተግባራዊነታቸዉን ማረጋገጥ ይገኝበታል፡፡
በምክር ቤቱ የሚቀርቡ የዕጩ ተሿሚዎችን የሚመለከቱ የውሳኔ ሃሳቦች የሴቶች ተሳትፎን በሚያበረታታ መልኩ እንዲቀርቡ በጎ ተጽዕኖ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአስፈፃሚ ተቋማት የዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ግምገማ ሂደቶች ላይ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል በምክር ቤቱ የረቂቅ
ሕግ ምርመራ ወቅትም ትኩረት የተሰጣቸው የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲካተቱና የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ መድረኮች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ሴት አመራሮችን በተለያዩ በምክር ቤት የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ ከባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አንዱ የሆነዉን የሴቶች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና የምክክር መድረኮች ለሴት የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር ም/ቤቶች አባላትና ለተባባሪ ወንድ የምክር ቤት አባላት መስጠት ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ኮከሱ ስራዉን በአገባቡ ለማከናወን እንዲችል የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ የግብረሠናይ ድርጅቶች ጋር የጋራ መግባባት ሰነድ በመፈራረም የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ አስገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብርና በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ስርጭት ወቅት የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸዉ የተለያዩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት ረገድ እንዲሁም ውጤታማ ለማድረግና ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረጉ ሥራዎችን በመሥራት በኩል ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ በአጠቃላይ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን በምክር ቤት ደረጃ አንጥሮ በማውጣት የሚከናወኑ ሥራዎች ላይ ጉልህ ክፍተት

ስለሚስተዋል ተገቢ ማስተካከያ ተደርጎ ራሱን የቻለ የምክር ቤት የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን መለየት በአዲስ አተያይ እንዲቃኝ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 2.7. የአቅም ግንባታ ተግባራት አፈፃፀም

የፓርላማ ዲሞክራሲ አሠራር እና ሥርዓት ተግባራዊነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአቅም ማጐልበት ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም መሠረት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ከተልዕኮ ጋር በተሳሰረ መልኩ ራሱን የቻለ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም በመቅረፅና በማደራጀት ሪፎርሙን የተከተለ አዲስ የአቅም ግንባታ ስልት በመከተል በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ተሰጥቷል፡፡ ከም/ቤቱ ውጪ ባሉ አካላት ጋባዥነት በተዘጋጁ የስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችም የቋሚ ኮሚቴዎች አመራርና አባላት ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ቋሚ ኮሚቴዎች ከራሳቸው ተልዕኮ በመነሳት የሚያዘጋጇቸውን የእርስ በርስ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና በሌሎች ስልጠናዎች የተሳተፉ አባላት ለሌሎች ቀሪ አባላቶቻቸው ያገኙትን ግንዛቤ የሚያካፍሉበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ የምክር ቤት አባላት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ምርጥ ልምዶችን የመለየት፣ የመቀመርና የማስፋፋት ተግባራት በዕቅድ ቢያዝም ተግባራዊ አልተደረገም:: የተሰጡ ስልጠናዎችን ፋይዳ  አስመልክቶ ግምገማ ለማድረግ የታቀደዉ ዕቅድ ተግባራዊ አልሆነም::በተጨማሪም የስልጠና ቦታ አመቺ አለመሆን፣ በአንድ አዳራሽ ውስጥ ሁሉንም አባላት ለክትትል በማያመች መልኩ ስልጠና መስጠት፣ የሥልጠና ድግግሞሽ መኖር፣ ለምክር ቤቱ የማይመጥን ስልጠናና አሰልጣኝ መኖር፣ በቂ የውይይት ጊዜ አለመኖር፣ ወዘተ የተለዩ ችግሮች ሲሆኑ በቀጣዮቹ ዓመታት በቂ ዝግጅት የተደረገባቸው ስልጠናዎችና አሰልጣኞች መኖር እንዳለባቸው ተመላክቷል፡፡

## 2.8. የመስክ ምልከታ ዋና ዋና የትኩረት ነጥቦች

ቋሚ ኮሚቴው የመስክ ምልከታ የሚያካሂደው የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን በብቃት ለማከናወን በተመረጡ ቦታዎች በአዲስ አበባ ዙሪያና በክልሎች) በአካል በመገኘት መደበኛና በድንገተኛ ምልከታያደርጋል፡፡ አስፈፃሚ ተቋማት በሕግ የተሰጣቸውን ተግባራት በስትራቴጂ ዕቅዳቸው ያስቀመጧቸውን ግቦችና ተግባራት አፈፃፀም፣ በቋሚ ኮሚቴዎች በየጊዜው የሚሰጣቸው ግብረ-መልስ ተከትሎ የተሠሩ ሥራዎችን፣ በመስክ ምልክታ የመከታተል ሥራ የሚሠራ ሲሆን በዚህም የተሰጧውን ተግባራቶች በተመለከተ የመከታተልና የመገምገም ሥራ

የሚሠራ ሲሆን ተቋማዊ ቁመና ከተሰጠው ኃላፊነትና ተግባር አኳያ መደራጀቱ፣ የመንግሥት በጀት አጠቃቀም፣ በተግባራቶች የሚለኩና የሚታዩ ውጤቶች ምን እንደሚመስሉ፣ አመራሩ የሚያደርጋቸውን ውስጣዊ የክትትልና ድጋፍ ሥራ፣[2] በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ አስተያየቶችን ተከትሎ የተወሰዱ ማስተካከያዎችና ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ ማስተካከያዎችና ችግሮቹ መፈታታቸውን ቋሚ ኮሚቴዎች የክትትልና ግምገማ ሥራዎች በመስክ ምልከታ ይሠራሉ፡፡

## 2.9. የመራጭ ህዝብ ውክልና ሥራን በተመለከተ

አባላት ወደ መረጣቸው ህዝብ ሲሄዱ አንድ ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር ቼክ ሊስት በማዘጋጀት እና አጭር ገለፃ /ኦረንቴሽን/ በመስጠት፣ ከክልሎች ጋር በማስተሳሰር በአመት ሁለት ጊዜ የማሰማራት ተግባር ተከናውኗል፡፡ የም/ቤት አባላት ከመረጣቸው ህዝብ የተነሱ ዋና ዋና ጥያቄዎችና ጥቆማዎችን በአግባቡ በማደራጀት ለሚመለከታቸዉ አካላት እንዲደርስ ጥረት መደረጉ በጥንካሬ የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱ ጥንካሬዎች ቢኖሩም በምክር ቤቱ የህዝብ ውክልና ሥራ ተግባራዊ የሚደረግበት በጥናት የተደገፈ አሠራር እና አደረጃጀት አለመኖሩ፤ በተለያዩ ምክንያት የውክልና ሥራቸዉን በአግባቡ የማይወጡ አባላት መኖራቸው እንዲሁም ከህዝብ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኝ በማድረግ በኩል እጥረት መኖሩ እና መልስ የሰጡትም ቢሆን በመሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር ያለ መጣጣም ችግር የነበረበት መሆኑ የታዩ ክፍተቶች ነበሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኮቪድ-19 ወረርሽኝና የጸጥታ ችግሮች ለህዝብ ውክልና ሥራ አፈፃፀም አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥረው አልፈዋል፡፡ ስለሆነም የህዝብ ውክልና ሥራዎች የህዝቡን እና የአባላትን ፍላጎት ባሟላ መልኩ የተከናወነ ነው ማለት አይቻልም፡፡

## 2.10. የዲፕሎማሲ ሥራን በተመለከተ

የሀገራችንን ተሰሚነት ከፍ ለማድረግ እንዲቻል በዓለም ዓቀፍ ደረጃ እና አካባቢያዊ የዲፕሎማሲ መድረኮች ላይ በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊና ሌሎች የትኩረት መስኮች ተሳትፎዎች ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሠረት የወዳጅ አገራትና አቻ ፓርላማዎችን የትብብር አድማስ ለማስፋት የሚያስችል እና የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና ሀገራት መሪዎችና ተጠሪዎቻቸው በምክር ቤታችን በመገኘት ያደረጓቸውን ጉብኝቶች፣ ሰላምንና ዴሞክራሲን መሠረት ያደረጉ ትብብሮች፣ በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሄዱ የሚገኙ ለውጦችን

ከግምት ውስጥ ያስገባ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ዓውድ እንዲኖር ለማስቻል የተለያዩ የግንኙት አውታሮችን በመጠቀም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ዕውቅና የተሰጠው ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የጥናቱ ዘዴ (Research method)

### 3.1. የአጠናን ዘዴ (Method)

የዚህ ጥናት ዓላማ የኢፌዴሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሉት 10 ቋሚ ኮሚቴዎች ባለፉት 6 የሥራ ዓመታት የነበሩ አጠቃላይ የሥራ ሂደቶችና የነበሩ ጥንካሬዎችና ክፍተቶችን መዳሰሳ እንዲሁም በቀጣይ ለሚመጣው ምክር ቤት አጠቃላይ ለሚያከናወናቸው ሥራዎች ስኬታማነት የሚያግዙ ግብአቶችን እና ተሞክሮችን ለማደራጀት ነው:: ይህንን ዓላማ ከግምት በማስገባት ጥናቱ የተከናወነበት ዘዴ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 3.2. ጥናቱ የተከናወነበት ቦታ (Study area)

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚያከናውናቸው ሁሉም ተግባራት በዋናነት የሚያተኩሩት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተዋቀሩ ቋሚ ኮሚቴዎች እና በፌደራል ደረጃ የተዋቀረው የአስፈጻሚ አካላት ላይ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት ውጤት በዋናነት ዓላማው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች በሕግ የተሰጣቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ የቆዩበትን ሂደቶች መዳሰስ፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ባለፉት 6 ዓመታት የነበሩአቸው ጠንካራ የሥራ ሂደቶችን መፈተሽ እና በሥራ ሂደታቸው ወቅት የነበሩ እጥረቶችና ቀጣይ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማተኮር ነው፡፡

### 3.3. የመረጃዎች ዓይነትና ምንጭ (Data type and source)

ይህ ጥናት የተከናወነው የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ የሚባሉ የመረጃ ዓይነቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ነው:: በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ በቀጥታ የተሰበሰቡ ሲሆን ይህም የመረጃ ዓይነት የተመረጠበት ምክንያት የዳሰሳ ጥናቱ ባህሪ (nature) ጥልቅ የሆነ መረጃን የሚፈልግ በመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ደግሞ ምክር ቤቱ በተከናወኑ አጠቃላይ ሥራዎች ላይ የነበሩ ጥንካሬዎች እና እጥረቶች እንዲሁም መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ሁሉንም ዓይነት የታተሙም ሆነ ያልታተሙ ዶክመንቶች እንዲሁም በቅርብ በምክር ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት የምክር ቤቱ ሥራዎች አስመልክቶ የተሠሩ የጥናት ሰነዶችን በማሰባሰብ ነው::

የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ከተሰበሰቡበት መንገዶች አንዱና ዋነኛው በጥናቱ እንዲሳተፉ የምክር ቤቱ አመራሮች እና አባላትን የቃለ መጠይቅ በማድረግ የተገኘ የመረጃ ዓይነት ሲሆን የተለየ አስገዳጅ ሁኔታ ስላልገጠመን የቃል መጠይቆቹ የተዘጋጁት በአማረኛ ቋንቋ ብቻ ነው:: ቃል መጠይቁ ለተደረገላቸው የምክር ቤቱ አመራሮች እና አባላት በቅድሚያ የጥናት ሥነ ምግባርን መሠረት ባደረገ መልኩ ስለጥናቱ ዓላማ ማብራሪያ የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ ፍቃደኛነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በዚህም መሠረት ጥያቄዎቹን በቃል በማቅረብ ተከናውኗል፡፡

## 3.4. የአጠናን ስልት

ጥናቱ ዓይነታዊ የጥናት ስልት (qualitative approaches) በመከተል ነው:: የqualitative አጠናን ዘዴ በእያንዳንዱ የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዙር የሥራ ዘመን በ6 ዓመት ቆይታው በሕገ መንግሥቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሕግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን መከታተልና መቆጣጠር፣ የውክልናና የዲፕሎማሲ ተግባራትን በተመለከተ በጥናቱ የተካተቱ የመረጃ ምንጮች ግላዊ አተያይ አመለካከት እንዲሁም ጠባይን ለመረዳትና ለመመዘን እንዲያስችል በማሰብ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን በጥልቀጥ እነዚህን የሥራ ሂደቶች ለመፈተሽና በሂደቱም የነበሩ ጥንካሬዎችና ክፍተቶች ለመዳሰስና ለመረዳት ብሎም ቀጣይ አቅጣጫን ለማመላከት የታሰበ ሲሆን በመጠይቁ እንዲሁም ከዶክመንት የተሰበሰቡ መረጃዎች ዓይነታዊ የጥናት ስልቶችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡

## 3.5. የናሙና አወሳሰድና የናሙና መጠን (Sampling techniques and size)

በዚህ ጥናት ዓይነታዊ የጥናት ዘዴ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ውጪ ሁሉም (10ሩም) ቋሚ ኮሜቴዎችን ያሳተፈ ሲሆን እነዚህም ከሴቶች ወጣቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከሰው ሀብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከገቢዎች በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከውጪ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከከተማ ልማት ኮንስትራክሽንና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከግብርናና አርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከተፈጥሮ ሀብት መስኖ እና ኢነርጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የጥናቱ አካል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በእነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች ካሉ አመራሮች፣ ከተመረጡ የምር ቤቱ አባላት እና የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ባለሙያዎች ጋር /Random Sampling/ በመጠቀም ቃል መጠይቅ የተደረገ ሲሆን እነዚህ ኮሚቴዎች እና ባለሙያዎች ከሚጠቀሙባቸው ዶኮመንቶች/ቼክ ሊስቶች፣ ሪፖርቶችና ግብረ መልስ ሪፖርት ሰነዶች/ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በአጠቃላይ ከሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ የቃለ መጠይቁ መልስ ሰጭዎች መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ሆኗል፡፡ ከእነዚህ የመጀመሪያና የሁለተኛ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች የትረካ ታሪክን የሚነግር የትንተና ስልትን /Narrative approach/ በመጠቀም የጥናቱ ውጤት በቀጣዩ ክፍል ቀርቧል፡፡

### 3.6. የመረጃ ትንተና እና አቀራረብ ስርዓት (Data analysis and presentation)

ለዚህ ጥናት ግብዓት እንዲሆኑ በተለያዩ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ የተሰበሰቡ መረጃዎች በዓይነት በዓይነት እንዲደራጁ ከተደረገ በኋላ የትረካ የመረጃ ትንተና ዘዴን (Narrative analisis approach) አማካኝ ውጤት በመጠም እንዲተነተኑ ተደርጓል፡፡ በቃል መጠይቁ የተገኙ የትንተና ውጤቶችን ለማጠናከር ከዶኩመንቶችና ሰነዶች የተሰበሰቡ መረጃዎች በየዘርፋቸው ማለትም በሁሉም የቋሚ ኮሚቴዎች የሥራ ክንውኖች ዙሪያ የነበሩ ጥንካሬዎች፣ እጥረቶችና ለቀጣይ መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች ላይ እነደዚሁም የጥናቱ ተሳታፊዎቹን አስተያየቶች በግብዓትነት መጠቀም የሚሉት ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የጥናት ውጤቶችና መረጃ ትንተና /Research result and Discussion/

በዚህ ጥናት 20 የሚሆኑ ከ10 ቋሚ ኮሚቴዎች አመራርና አባላት እንዲሁም 15 ከተለያዩ የምክር ቤቱና የምክር ቤቱ ጽ/ቤት የሥራ ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በቃለ መጠይቁ የተሳተፉ ሲሆን በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለፉት 6 የሥራ ዓመታት በቋሚ ከሚቴዎች የሚተገበሩ ሕግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች መከታተልና መቆጣጠር፣ የመራጭ ሕዝቦች ውክልና እና የዲፕሎማሲ ተግባራት ሥራዎችን አስመልክቶ የነበሩ ጥንካሬዎችና እጥረቶችን እና የማስተካከያ እርምጃዎች በዳሰሳ ጥናቱ ለማየት ተሞክሯል፡፡ የቃል መጠይቆችን በመጠቀም ከቋሚ ኮሚቴዎች አመራሮችና አባላት፣ ምክር ቤቱ ጽ/ቤት ባለሙያዎች እና ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፣ የቋሚ ኮቴዎች አመራሮች እና አባላት የሚጠቀሙባቸው ቼክ ሊስቶች፣ የግብረ መልስ ሪፖርት ፎርማቶች፣ የቋሚ ኮሚቴዎቹ ዕቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ታይተዋል፡፡

ከእነዚህ መልስ ሰጭዎችና ዶክመንቶች የተገኙ ውጤቶች እንደሚከተለው የቀረቡ ሲሆን የተገኙትን የጥናት ውጤቶች ከተዛማጅ ጽሁፍ ዳሰሳች ጋር በማስተሳሰር የጥናት ትንተናዎች አብረው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. ምክር ቤቱ በ5ኛው ዙር በ6 ዓመት የሥራ ቆይታው ሥራዎችን ሲያከናውንበት የነበረው አጠቃላይ የሥራ ሂደትን በተመለከተ

#### ሀ. በጥንካሬ የታዩ

በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 እና በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ መሠረት በዋና ዋና ተልእኮች ላይ ትኩረት በማድረግ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል፡፡ ሕግ የማውጣት፣ ክትትልና ቁጥጥር፣ የመራጭ ሕዝቦች የውክልና ሥራዎች እና የዲፕሎማሲ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በደንቡ መሠረት አማካሪ ምክር ቤት፣ ቋሚ ኮሚቴዎችና እና ንዑሳን ኮሚቴዎች ተደራጅተው በየራሳቸው ዕቅድ አዘጋጅተው ከአባላት ጋር የጋራ በማድረግ ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማከናወን ችለዋል፡፡ አባላት እርስ በእርሳቸው ተናበውና

ተደጋግፈው የተሰጣቸውን ተልዕኮ መወጣት መቻቸው፣ በሥራ አፈፃፀም ሂደት የሚገጥሙ ችግሮችን በውይይትና በመረዳት መንፈስ መፍትሄዎቻቸውን በማስቀመጥ ዕቅዶቻቸውን ለማሳካት ችለዋል፡፡ ምክር ቤቱ የ5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ እና ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት በየደረጃው ውይይት በማካሄድ የሚሰጡ አስተያየቶችን በማካተት የምክር ቤቱ መሪ ዕቅድ አፅድቆ ወደ ሥራ መገባቱ ይታወሳል፡፡

የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀት ወደ 20 ተፈጥረው በእያንዳንዱ ሥር ሰብሳቢና ም/ሰብሳቢ፣ ንዑስ ኮሚቴ ተፈጥሮ ከ15 እስከ 25 አባላት ያሉት ሆኖ ጠቅላላ የፌዴራል ተቋማትን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 72 (2) 77(1-13) መሠረት ተከፋፍለው ከምክር ቤቱ ዕቅድና ከተቋማት ኃላፊነት አንፃር በየኮሚቴ ዕቅድ ተዘጋጅተው በአባላትና በም/ቤቱ እንድፀድቅ መደረጉ፡፡ በዕቅዳቸው መሠረት መገምገሚያ ቼክሊስት በማዘጋጀት የክትትል ቁጥጥርና ድጋፍ ስራውን የተቋማትን እስትራቴጂክ እና ዓመታዊ ዕቅድ፣ የየሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በመመርመር፣ ለኮሚቴውና ለም/ቤት ሪፖርታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ በዕቅድ የሚመራና ድንገተኛ የመስክ ምልከታ በማድረግ የተገኙ ግኝቶችን ለተቋማት እና ለምክር ቤቱ ግብረ-መልስ በመስጠት እየተሠራ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ከ2011 ጀምሮ የቋሚ ኮሚቴ አደረጃጀትን በመከለስ 10 ቋሚ ኮሚቴዎችና 33 ንዑስን ኮሚቴዎች ተደራጅተው ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

በዚህም መሠረት ቋሚ ኮሚቴዎች ከምክር ቤቱ መሪ ዕቅድና ከሚከታተሏቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ዕቅድና ከተሰጣቸው ተልዕኮ በመነሳት መነሻ አድርገው የራሳቸውን ዕቅድ አቅደው ከአባላት ጋር የጋራ በማድረግና በማጽደቅ ለአፈጉባዔ እና ለመንግሥት ተጠሪ ልከዋል፡፡ በቋሚ ኮሚቴዎች ሥር የተደራጁ የንዑሳን ኮሚቴዎች ከቋሚ ኮሚቴዎች ዕቅድ በመነሳት የራሳቸውን ዕቅድ አቅደው ወደ ተግባር የገቡ ሲሆን፣ ከመንግሥት ተጠሪ በኩል ለቋሚ ኮሚቴዎች በዕቅዳቸውና በዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርታቸው ላይ ግብረ መልስ እየተሰጠበት ወደ ተግባር እንዲገባ ተደርጓል፡፡

ምክር ቤቱ የ6 ዓመት ቆይታው አንድ ወጥ ምስል ያልነበረው ሲሆን እስከ መጋቢት 24/2010 ዓመት ባሉት 3 ዓመታት ሀገሪቱ ውስጥ ተከስቶ በነበረው ሕዝባዊ ንቅናቄና መንግሥት ይወስደው በነበረው እርምጃ ምክንያት ምክር ቤቱ ለሥነልቦና ተፅዕኖ ተዳርጐ ነበር፡፡ ይህም ውሎ አድሮ የምክር ቤት አባላት የሕዝብን ንቅናቄ በይሁንታ መልክ በመውሰድና አቋማቸውን

በምክር ቤቱ ይገልፁ ስለነበር በሕግ አወጣጥና ክትትል ሥራቸው ላይ ተፅዕኖ አሳድሮአል፡፡ በሌላ መልኩ የውክልና ሥራቸውን ወደ ሕዝብ ወርደው ለመወጣት ያልቻሉ ሲሆን በታቀደው ዕቅድና በተገኘው ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት ለመመዘንና በአካል ቀርቦ ለማየት ባመቻላቸው ሕዝቡ በዚህ ጉዳይ "ተረስቻለሁ» በሚል ስሜት እንዲፈጠርበት ምክንያት ሆኗል፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች የዕቅዳቸው ማስፈፀሚያ ቼክ ሊስት አዘጋጅተው አስፈፃሚ መ/ቤቶች ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን ምክር ቤቱ የ6 ወራት እና የዓመቱ ማጠቃለያ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ በማቅረብ ውይይት በማድረግ የተሰጡ አስተያየቶችን በማካተት ሪፖርቱ እንዲፀድቅ አድርጓል፡፡

## ለ. በእጥረት የታዩ

በምክር ቤቱ  የአሠራርና የአባላትሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 በተሻሻለው አንቀፅ 4(2ና3) በሚተደነገገው መሠረት ኃላፊነቱን የግልፀኝነት፣ የተጠያቂነት የአሳታፊነት መርህን በተከተለ መንገድ የሚሠራ አለመሆኑ፡፡ ለአብነት፡- ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በምክር ቤቱ ስትራቴጂ ዕቅድም ይሁን ዓመታዊ ዕቅድ ላይ ለአገሪቱ ህዝብ ተጠሪ እና የሥልጣን የበላይ አካል የሆነ ከምክር ቤቱ አባላት ጋር ውይይት አለመደረጉ፣ የምር ቤቱን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመት ወይም በ6 ወር በጋራ መገምገም አለመቻሉ፡፡ የምክር ቤቱ አባላትና አመራር ከጉባዔ ስብሰባዎች ውጪ በዕቅድ የሚመራ የውይይት ጊዜ አለመኖር፡፡

የኢፌዲሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 (4) የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት የመላው ህዝብ ተወካዮች ናቸው ተገዥነታቸውም ለሕገ-መንግሥቱ፣ ለህዝቡ እና ለህሊናቸው ብቻ ነው፡፡ የሚለውና በ54 (5) ማንኛውም የም/ቤት አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም የሚለው ሕገ-መንግሥታዊ መርህ ከለውጡ በፊትም ሆነ በኋላ ተግባራዊ እየሆነ አለመሆኑና የሀሳብ ልዩነት ከመጣ ተከራክሮ አሸናፊ ሀሳብ የማስተናገድ ጉዳይ በተግባር የሌለ መሆኑ፡፡

በኢፌዴሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 45 የተገለፀውን ሥርዓተ-መንግሥት ግንባታ በፌዴራሊዝም ሥርዓት ግንባታ ጉዳይ በምክር ቤቱ በተግባር የሌለ መሆኑ፣ በኢፌዲሪ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 50(3) የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ህዝብ ነው፡፡ የሚለው በምክር ቤቱም

በመንግሥትም እስከ 5ኛው ፓርላማ ድረስ ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑና በተግባር ሲታይ የሥልጣን የበላይ ሕግ አስፈፃሚውና ተርጓሚ አካላትና የምክር ቤቱ አመራር መሆናቸው እና ተጠሪነታቸውም በተግባር ለእነዚህ አካላት የሚመስላቸው መሆኑ፡፡

በኢፌዴሪ በሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 (16) በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ሳያቆም ሲቀር በራሱ አነሳሽነትና ያክልሉ ፈቃድ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ ለፌደሬሽንና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በተደረሰበት ውሳኔ መሠረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል፡፡ የሚለው ድንጋጌ የማይፈፀም መሆኑ፣ የኢፌዴሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 103 መሠረት አስቸኳይ ጊዜ ዓዋጅ መንግሥት ሀገረ-መንግሥቱና ሕገ-መንግሥቱ አደጋ ላይ መሆኑን አምኖ ሲያሳውጅ በመርማሪ ቦርድ በኩል በአግባቡ አለመመርመርና ምክር ቤቱም ትኩረት የማያገኝ መሆኑ፡፡

የኢፌዴሪ በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 104(2) መሠረት የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች በሚያደርገው የብድርም ሆነ የእርዳታ ወጪ ድጎማ ኦዲትና ቁጥጥር አለመደረጉ፣ በአጠቃላይ እንደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ማዕከል ያደረገ ሕገ-መንግሥታዊ ተልዕኮ ከመፈፀም ይልቅ በሥልጣንና ራስን ማዕከል በማድረግ የመጠቃቀምና የመጠቃቃት ሥራ ላይ ትኩረት የተደረገበትና በምክር ቤቱ አሠራርና በአባላት ሥነ ምግባር ደንቡ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ ያለማድረግ ሁኔታ ይታያል፡፡

በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላትሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ለአባላት የስብሰባ/የውይይት/ አጀንዳ ከ48 ሰዓት በፊት ለምክር ቤቱ አባላት ይደርሳል የሚለው ተግባዊ አለመደረጉ፣ አባላት በኮሚቴ ሥራም ሆነ በምክር ቤቱ መደበኛ፣ አስቸኳይና ልዩ ስብሰባ ተሟልቶ አለመገኘት፣ የተገኘ እና ያልተገኘ አባል ተለይቶ አለመታወቁ፡፡ በዚህም በሚካሄዱ ስብሰባዎች ከምክር ቤቱ 547 አባላት መካከል ከ200 እስከ 250 አባላት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ እየተገኙ በመሆኑ አልፎ አልፎ የምክርቤቱ ኮረም ያለመሙላት ችግር የሚያጋጥም መሆኑ ይህንንም ለማረም እና የሚቀሩ አባላትን በተመለከተ ምንም የማስተካከያ ሥራ አለመሠራቱ፡፡

## 4.2. በምክር ቤቱ በተሠሩ ሥራዎች ዙሪያ የነበሩ ጥንካሬዎችና እጥረቶችን በተመለከተ

### 4.2.1. የሕግ ማውጣት ሥራን በተመለከተ

**ሀ. በጥንካሬ የታዩ**

ለምክር ቤቱ የተላኩ ረቂቅ ሕጎችን በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ለምክር ቤቱ ቀርቦ የመጀመሪያ ምንባብ ተደርጎና በአባላት አስተያየትና ጥያቄ ቀርቦበት ለዝርዝር እይታ ሕጎቹ ለሚመለከታቸው ለቋሚ ኮሚቴዎች ከተመራ በኋላ፣ ቋሚ ኮሚቴዎች በተመሩላቸው ሕጎች ላይ በሁለተኛ ንባብ ቀርቦ አባላቱ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎችን በማደራጀት አስረጂዎች እንዲቀርቡና በተነሱ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ተደርጎ ተጨማሪ ውይይቶች መካሄዳቸው፣ በተመሩት ረቂቅ ሕጐች ላይ በባለሙያ አሰተያየት እንዲሰጥበት ማድረግ መቻሉና ህዝቡ ቀርቦ ወይም በተለያየ ዘዴዎች አስተያየት እንዲያቀርብ በሚዲያ ጥሪ መደረጉና አስፈፃሚ ተቋማት ደግሞ ምላሽ እንዲሰጡና ረቂቅ ሕጉ ዳብሮ ለውሳኔ እንዲቀርብ መደረጉ በጥንካሬ የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦች በም/ቤቱ የህግ ባለሙያዎችና በዘርፉ ለተመደቡ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለቋሚ ኮሚቴው ከቀረበ በኋላ ለምር ቤቱ መቅረቡ የበለጠ በዚያ የስራ ዙሪያ ጥራት ያለው ስራ ለመስራት ማስቻሉ፡፡ በሕጎች ምርመራ ወቅት የህዝብና የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ጥረት የሚደረግ መሆኑ እና የሕግ አወጣጥ ሂደቱ በምክር ቤቱ የህግ ባለሙያ ቡድን የሚደገፍ መሆኑ፣

የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ማህተም ያልተደረገባቸው ረቂቅ ሕጎችን፣ የአስፈፃሚ አካላት ፊርማ የሌላቸውንና ከአገራችን ህጎች ጋር የሚፃረሩ ስምምነቶችን፣ የረቂቅ ሕግ ሂደቶችን ያላሟሉ ረቂቅ አዋጆችን ወደ መጣበት የመመለስና ሲስተካከል የሚመረምር መሆኑ፣ አብዛኛው አዋጆች በሥነ-ምግባር ደንቡ አንቀጽ 50(1-4) መሰረት እና 51(1-9) በአግባቡ ተመርምሮ በወቅቱ የሚፀድቅ መሆኑና ደንብና መመሪያ መውጣት ያለባቸው አዋጆችን አንቀጽ ተለይቶ ትኩረት በመስጠት የሚፀድቅ መሆኑ፣ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ይሁንታን የሚጠይቁ ሕጎች ሲሆኑ በጋራ ዕውቅና እንዲወጣ ለማድረግና ጊዜ ተወስዶ በጥልቀት ምርመራ የሚያስፈልጉ ሕጎች ሲሆኑ አፈ-ጉባዔውን እያስፈቀዱ በትኩረት ተመርምሮ የሚፀድቅበት ጊዜ በማራዘም የሚፀድቅ መሆኑ፡፡

አስፈፃሚው አካል ለስራው ያግዘኛል የሚሏቸውን ሕጎች በማውጣት በኩል ከቋሚ ኮሚቴዎች በኩል የተሠራው ሥራ ጥሩ ጅማሮ ያለው ሲሆን የበለጠ ተቋማት በተሰጣቸውን ሀላፊነት ስራቸውን ለመወጣዘት ያገዛቸው መሆኑ (የሰራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር)፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ሀገሪቱ ውስጥ በነበሩ አለመረጋጋቶች መሀል ሆኖም የሚጠበቅበትን ሕግ የማውጣትና የመከታተል ስራ በምክር ቤቱ የአሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ መነሻ ተደርጎ መተግበሩና እነዚህ የወጡ ህጎች የአስፈፃሚ ተቋማት ሥልጣንና ተግባርን መነሻ ያደረጉ መሆናቸው መልካም ጎኑ ሲሆን በሌላ በኩል የተለያዩ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ህጐች በመመርመር የማሻሻያ ሥራዎችን መሠራታቸው ሁለንተናዊ የህዝቦችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ እድገትን ለማፋጠን ያስቻለ ጉዳይ መሆኑ፡፡

### ለ. በእጥረት የታዩ

በቀርቡ ረቂቅ ሕጎች ላይ በተደረጉ ውይይቶች የባለ ድርሻ አካላትን ተሳትፎና የክልልሎች ተሳትፎ ዝቅተኛ ወይም አናሳ መሆኑና ባለ ድርሻ አካላቱ ተገኝተው አስተያየት ቢሰጡም ተቀብሎ የረቂቅ ሕጎቹ አካል አለማድረግ ችግር በስፋት የታየ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ለምክር ቤቱ ቀርበው አስፈላጊውን ሂደት አልፈው የጸደቁ ሕጎች ለሕዝቡ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ውስንነት መኖሩ እና ለወጡ ሕጎች አስፈላጊው ደንቦችና መመሪያዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ መውጣታቸውን አስመልክቶ የተደረጉ የክትትልና የቁጥጥሮች ስራዎች አናሳ መሆናቸው ታይቷል፡፡

በምክር ቤቱ ጽ/ቤት ያሉ የሕግ ባለሙያዎች የአቅም ውስንነትና የባለሙያ እጥረት የታየ ሲሆን አልቀው ለሕትመት የሄዱ እና የታተሙ ህጐች የእርምትና የቃላት ግድፈቶች በስፋት የተገኙባቸው መሆኑ፣ በቋሚ ኮሚቴ አባላት በኩል በወጡ ህጐች ዙሪያ የቴክኒክ እርምት እንጂ ፖሊሲን መሠረት ያደረገና ለሀገርና ለሕዝብ በሚጠቅም አግባብ እርምትና ማስተካከያ እንዲደረግ ግፊት አለመደረጉና ይህንን ለመፈፀም የአባላት ቁርጠኝነት አናሳ መሆኑ፣ አባላቱም በሕጉ ዙሪያ ያላቸው ዕውቀትና የክህሎት ደረጃ ክፍተት ያለበት መሆኑ፡፡

በተለያዩ ጊዜያት የወጡ ረቂቅ ሕጎች ላይ የሕዝብ አስተያየትና ተሳትፎን በሚመለከት በሚዲያ የሚተላለፉ የጥሪ መልእክቶች የአየር ሰዓት ወይም ቀናት ያነሱ መሆናቸው በጉዳዩ ላይ ያገባኛል ብሎ በውይይቱ የሚሳተፍ አካል በሚፈለገው ደረጃ እንዳይገኝ ማድረጉ፣ በወጡት ግጎች ዙሪያ የአተገባበር ክፍተትን በመፍጠር ሕጎች ቶሎ ቶሎ እንዲሻሻሉና የወጣውን ሕግ

በጥብቅ ዲሲፕሊን በመፈፀም በኩል መጠነ ሰፊ ችግሮች በአስፈፃሚው አካል ላይ መታየት መቻላቸው፡፡

ከቋሚ ኮሚቴዎቸ አባላት ጋር ተያይዞ በተለያዩ በግል አጀንዳዎች /የብሄር፣ የሀይማኖት፣ ወደ ተወከሉበት አካባቢና ክልል፣ ቦታን /ያተኮሩ ጉዳዮች ላይ የመጠመድ ሁኔታ፣ ብሎም ስብሰባ ላይ አለመገኘትና አቋርጦ መውጣት ከመከሰቱም በላይ በስብሰባው ላይ የተገኙ አባላትም ሰነዶችን በአግባቡ አንብቦና ተዘጋጅቶ የመምጣቱ ሁኔታ በጣም ያነሰ መሆኑ ሊታወቅ ችሏል፡፡

## 4.2.2. የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን በተመለከተ የታዩ ጥንካሬዎችና እጥረቶች

### 4.2.2.1. የተቋማትን ዕቅድና የዕቅድ የአፈፃፀም ሪፖርት ሥራን በሚመለከት

**ሀ. በጥንካሬ የታዩ**

አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የሚልኳቸውን ዕቅዶች የመገምገም ሂደትን በተመለከተ በዕቅዳቸው ውስጥ የሁኔታ ግምገማ፣ የአመራር፣ የፈፃሚ፣ የባለድርሻ አካላት ሚና በጥንካሬና በእጥረት፣ የነበሩ ማነቆዎችና መፍትሔዎቻቸው፣ ቁልፍ ችግርና ተግባር፣ ግልፅ ግቦች የተቀመጠና የ2ኛውን ዕትዕ/ስትራቴጂ ዕቅድ/ ግቦችን ለማሳካትና ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ የተጣጣመና የተገናዘበ መሆኑን የማረጋገጥ፣ እንዲሁም የሚያሠራ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይልና በጀት መመደቡን ማረጋገጥ፣ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ዕቅዳቸውን ሲያቅዱ የመነሻ ሁኔታዎችንና የሥራ አካባቢውን በሚገባ ተገምግሞና ተተንትኖ የተዘጋጀ መሆኑን የማየትና የመገምገም ሥራዎች ተሠርተዋ፡፡

አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ምክር ቤቱ ያጸደቀላቸውን መደበኛና ፕሮግራም በጀቶችን የሚገልጽ የድጊት መርሃ ግብር በየሩብ ዓመቱና በየዘርፉ ተከፋፍሎ ለክትልና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ መዘርዘሩን ማረጋገጥ፣ የአስፈፀሚ መሥሪያ ቤቶቹንና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ሀብትና ንብረት በቁጠባ ለመተግበር የሚያግዙ ግልፅ አሠራሮችን ተለይተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ፣ ዕቅዳቸው ባለድርሻ አካላትን የለየና የግንኙነት አግባብን ያስቀመጠ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በአፈፃፀም ላይ ለሚፈጠሩ ክፍተቶች/ችግሮች/ ለመለየትና ለመቀበል እንዲሁም አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የተለዩ ምቹ ሁኔታዎችና የአሠራር ሥርዓቶች መኖራቸውን እና ፈጣን መፍትሄ ለማስቀመጥ የሚያግዝ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመርና

ለማስፋት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዕቅድ ክለሳ ለማድረግና ፈጣን ምላሽ /ግብረ መልስ/ ለመስጠት የሚያስችል አሠራር መኖሩን የማረጋገጥ ሥራ መሠራቱ፡፡

አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማቶች የበጀት አጠቃቀማቸውን በሚመለከት ከብልሹ አሰራር የፀዳ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መኖሩን፣ ከምክር ቤቱ እና ከሌሎች ባለድሻ አካላቶች የሚሰጣቸውን ግብረ መልሶች፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችን እና ለሚነሱ ህዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የአሠራ ሥርዓት መዘርጋቱን፣ ዘርፈ ብዙ ስራዎች /የሴቶች ጉዳይ፣ HIV/Aids፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች፣ የአካል ጉዳተኞች እንደየ ሥራ ባህሪያቸው ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ አሠራሮች በዕቅዳቸው መካተታቸውን፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል አግባብ የዕቅዳቸው አካ መደረጉንና ለዚህም ማስፀሚያ የሚሆን አደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት መኖሩን የማረጋገጥ ተግባራትን ማከናወናቸው፡፡

የሚቀርቡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች ከታቀደው ስትራቴጂ ዕቅድ፣ ከዓመቱ ዕቅድ፣ ከተጣሉ ግቦችና ተግባራት ጋር ተነፃፅረው የደረሱበትን የአፈፃፀም ደረጃ በግልፅ በሚያመላክት አግባብ የቀረቡ መሆናቸውን፣ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ በቀጣይ ሊኖሩ በሚችሉ የለውጥና ሪፎርም ስራዎች ጋር በተያያዘ በጥናት የተዘጋጁና የታቀዱ አሠራሮች ተግባራዊ መደረጋቸውን፣ የመሥሪያ ቤቶቹንና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ሀብትና ንብረት ከኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት በፀዳ መልኩ ለመተግበር የሚያግዝ ግልፅ አሰራሮችን ለይቶ መታቀዱንና አፈፃፀሙም በሪፖርታቸው በንጽጽር መቅረቡን፣ በዋና ኦዲተር የተሰጡ የኦዲት ግኝቶችና የተሠጡ አስተያየቶችን ተከትሎ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውንና በወቅቱ ለዋና ኦዲተር ሪፖርቱ መላኩን ማረጋገጥ፣ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ የታቀዱ ዕቅዶችን ለማሳካት እና ዘላቂ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ የሚያስችል እና የህግ ማዕቀፍ ክፍተቶችን መሙላት፣ ደንብና መመሪያ ያልወጣላቸው እንዲወጣላቸው በማድረግ ተፈጻሚነታቸውንና የአስፈፃሚ አካላት ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑን፣ የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ተጠያቂነትን ማስፈን በሚቻል ደረጃ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፣ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች /የሴቶች ጉዳይ፣ HIV/Aids፣ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች፣ የአካል ጉዳተኞች እንደየስራ ባህሪያቸው ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉ ግልፅ ዕቅድ መታቀዱንና አፈፃፀሙም በሚቀርቡ ሪፖርቶች ውስጥ በንጽጽር መቅረቡን እና በቋሚ

ኮሚቴዎች ለተሰጡ ግብረ መልሶች አስፈላጊውን ማስተካከያ መደረጉን የማረጋገጥ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸው፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች ከዚህም በተጨማሪ በፅሑፍ የቀረበውን አፈፃፀም ለመገምገም የከተማ፣ ከከተማ ውጭ እና ድንገተኛ የመስክ ምልከታ ፕሮግራም በማዘጋጀት በአካል ምልከታ መደረጉ በአስፈፃሚው አካል የተሰሩ ተጨባጭ የሆኑ ሥራዎችን ለመዳሰስ ያስቻለ ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት የተቋማቱ እቅድ አፈፃፀም በመሬት ላይ ምን ተጨባጭ ለውጥ እንዳለው ለመገምገም በማስቻሉ የህዝቡ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለመረጋገጥ እድል ፈጥሯል፡፡

## ለ. በእጥረት የታዩ

ቋሚ ኮሚቴዎች የአስፈፃሚ አካላትን እቅድና ሪፖርትን በሚገመግሙበትና አስተያየት በሚሰጡበት ጊዜ በተለመደው የአሠራር አካሔድ ለመሔድ የመፈለግ አዝማሚያ፣ (አዲስና የተሻለ የክትትልና ቁጥጥር የአሠራር ሥርአትን ለመዘርጋት ያለው ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑ)፡፡ የሚከታተሏቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች አልፎ አልፎ የመዘግየት ሁኔታ ቢኖርም በአባላቱ በኩል በተገቢው ጊዜ ሰነዱን አይቶ ለተቋማቱ ግብረ መልስ ለመላክ ያለው ውስንነት፣ በክትትልና ቁጥጥር ሥራ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች በቋሚ ኮሚቴዎች የሚሰጣቸውን ግብረ መልስ በግብዓትነት ስለመጠቀማቸውና እንዲሻሻሉ አቅጣጫ የተሰጡባቸውን ተግባራቶች መስተካከላቸውን በአባላቱ ክትትል የማድረጉ ሁኔታ ያን ያህል ጎልቶ ያለመታየቱና ቢኖርም ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ ከማድግ አኳያ ጠንካራ የሆነ እንቅስቃሴ አለመታየቱ እንደ ክፍተት ታይቷል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎችን አባላት አስመልክቶ እንዲከታተሉት ከተሰጣቸው ተቋም ውጪ ከሁሉም ተቋማት የሚላከውን ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት ላይ አንብቦና ተዘጋጅቶ ያለመምጣት እና ያለመዘጋጀት ሁኔታ መኖር ይህም በቋሚ ኮሚቴው ደረጃ ለሚታዩ ተቋማት የግብረ መልስ አሰጣጥ ላይ ክፍተት መፍጠሩ፣ ምክር ቤቱ በክትትልና ቁጥጥር ወቅት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚያገኛቸውን እጥረቶች ማስተካከያ እንዲያደርጉ በቃልና በጽሑፍ ለአስፈፃሚ ተቋማት ከመስጠት ባለፈ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን ያልነበረው ሲሆን፡ ይህም ምክር ቤቱን «ጥርስ የሌለው አንበሳ» የሚል ስያሜን ያሰጠው ተግባር መሆኑ፡፡ ምንም እንኳን የድጋፍ ሰጭ ባለሙያዎች የአቅም ክፍተት እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ ኮሚቴዎች አብረዋቸው ያሉትን ድጋፍ ሰጭ ባለሙያዎች የሚሰጡትን አስተያየት አለመቀበል፣ ባለሙያዎች የተለያዩ

ተግባራትን ከሙያ አንፃር ሠርተው ሲያቀርቡ በቋሚ ኮሚቴው ስብሳቢ ወይም አባላት ካልሆነ በስተቀር የባለሙያ ሪፖርት አንሰማም፣ ማቅረብ የለበትም የሚል አስተሳሰቦችና ባለሙያን በተገቢ ሁኔታ ያለማሳተፍ ችግር የተንፀባረቁ መሆናቸውና ይህ ደግሞ የባለሙያውን ሞራል የሚነካ በመሆኑ በባለሙያ የሚከናወኑ ተግባራት ላይ ክፍተትን ለመፍጠር ችሏል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የመጡ የአስፈፃሚ ተቋማትን ቀድሞ በተዘጋጀው የቋሚ ኮሚቴዎች ዕቅድ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ያልተካሄደበት ሁኔታ በተደጋጋሚ የተስተዋለ ችግር ሆኖ፣ በየጊዜው የተላኩ የተቋማትን የዕቅድ አፈፃፀም ሁኔታን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራዎች በበቂ ሁኔታ ያለመሠራታቸው ጉዳይ፣ ችግር ያሉባቸው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችና በሥራቸው ያሉ ተጠሪ ተቋማት ላይ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ከማድረግ ይልቅ በቸልታ እንዲታለፉ በር የከፈተ ተግባር መሆኑ እና ክትትልና ቁጥጥር ለሚያደርጉ የቋሚ ኮሚቴ አባላቶች በቂ የሆነ ሎጂስቲክ፣ የልዩ ልዩ ግብዓቶችና አቅርቦቶች ያለመሟላታቸው እንደ እጥረት ተይዟል፡፡

### 4.2.2.2. የመስክ ሥራዎችን በሚመለከት

**ሀ. በጥንካሬ የታዩ**

ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች በክትትልና ቁጥጥር ሥራ ወቅት ተቋማት በዋናነት በ2ኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የተቀመጡ ግቦችን ከማሳካት አኳያ እያከናወኑት ስለነበረው ሥራና ዕቅዱንም ለማሳካት እየሠሩ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ሥራ በዋናነት መሥራት መቻላቸው፡፡ በእያንዳንዱ የመስክ ምልከታ ወቅት ለምልከታ የሚያስፈልጉ ቼክ ሊስቶችን፣ የመስክ መልከታ መርሃ ግብር፣ የመስክ ምልከታ ዓላማና ግቦች ተለይተው ዝግጅት ማድረግ መቻላቸውና የመስክ ምልከታ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ የምልከታውን ሪፖርትና ግብረ መልስ በቃል እና በጽሑፍ ለተቋማቱ የተሰጠ መሆኑ፡፡ በተጨማሪም በመስክ ምልከታ ሂደቱ ተቋማቱ በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተልዕኮ ምንነት እና ለማስፈፀም የተዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂ ዕቅድ፣ ደንቦችና ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣ የሰው ኃይል አደረጃጀት፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች መሠራታቸውን ከመገምገምና ለዕቅድ ማፈፀሚያ በጀት መያዙን በየሩብ ዓመቱ ዕቅዱና በጀቱ በተናበበ ሁኔታ መደልደሉን የማረጋገጥ ሥራ መሠራቱ፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች መንግሥት የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ ያስችለው ዘንድ የሚደረገው በጀኔራል ዋና ኦዲተር በኩል የመንግሥት ገንዘብ አያያዝ ላይ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን

በመለየት ግምገማ መደረግ መቻሉና የሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ ለመከታተል የሚያስችል የውስጥ ኦዲተር መሟላቱን የፌደራል ዋና ኦዲተር የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተ በተቋማቱ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን የመፈተሽ ሥራ መሠራቱ፡፡

ቋሚ ኮሚቴዎች በሚከታተሏቸው ተቋማት ያለውን የመልካም አስተዳደርና የሰው ሃብት አያያዝን እንዲሁም የቅሬታ ማስተናገጃና አፈታትን በተመለከተ ምልከታ ማድረጋቸውና የተቋማቱን ሠራተኞች በማወያየት በተቋማቱ ያሉ ችግሮችን የመለየትና አቅጣጫ የመስጠት ሥራ መሥራታቸውና፣የለውጥ አሠራርን ለማስረፅና መልካም አስተዳደር ለማስፈን በተቋማቶቹ ማኔጅመንት እና ሠራተኛው ፍትሐዊና ተጠያቂነት ያለበት የአሠራር ስርዓት ስለመዘርጋቱ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ወቅታዊ ምላሽ መሰጠቱን የማረጋገጥ ስራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ቋሚ ኮሚቴዎች የዲሞክራሲ ተቋማት አሠራር እና ተግባራትን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ መቻቸውና ለተቋማቱ በምክር ቤቱ የተመደቡ በጀቶች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ፣ በዕቅድ አፈፃፀም በሪፖርታቸው የተሠሩ ሥራዎችን በአካል በማየት ጥንካሬዎችና መስተካከል የሚገቡ ተግባራቶችን በመለየት የቃልና የጽሑፍ ግብረ መልስ መሥጠት መቻቸው፡፡

በአጠቃላይ በተደረጉ የመስክ ምልክታዎች የተቋማቱን ዕቅድና አፈፃፀም እንዲሁም ያስገኙትን ውጤት በተመለከተ ለተቋማቱ በምልከታ የተገኙ ግኝቶችን ጥንካሬና እጥረቶችን እንዲሁም በቀጣይ ተቋማቱ ሊያሻሽሉ ይገባሉ የተባሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በመለየት ለተቋማቱ ግብረ-መልስ መሰጠት መቻሉ የቋሚ ኮሚቴዎች በመስክ ምልከታ ስራዎች ላይ የነበሯቸው ጥንካሬዎች ናቸው፡፡

**ለ. በእጥረት የታዩ**

አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች በሕግ በተሰጣቸው ተልዕኮና ሥልጣን ልክ እንዲደራጁና የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዲያስገኙ ተደርገው ያለመደራጀትና በስልጣናቸው ልክ ተግባራዊነት እንዲኖራቸው አለመደረጉ፣ ለአብነት፡- የሠላም ሚኒስቴር እና የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ሥራ አመራር ኮሚሽን በምልከታ ወቅት የሚገኙ ግኝቶች ቢሆኑም ባለድርሻ አካላት ችግሩን ከመፍታት ይልቅ በዝምታና በመሸፋፈን የማለፍ ሁኔታ መኖሩ፡፡ የተደረጉ የመስክ ምልክታዎች ተቋማቱን ጥልቀት ባለው ሁኔታ የሚያይ ያለመሆኑና ተከታታይነት የጐደለው

እንዲሁም በምልከታውም ሆነ በአጠቃላይ ክትትል ቁጥጥር የተገኙ ግኝቶች ላይ ጠንካራ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ከማድረግ አንፃር ገፍቶ ያለመሄድ ችግር መኖሩ እንደ ክፍተት የሚጠቀስ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴዎች በተቋማት በሚያደርጉት የመስክ ምልከታ ወቅት የተቋማቱን ተልዕኮና ሥልጣን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ያለመኖሩና ግንዛቤ እንዲኖራቸው የአቅም ግንባታ ስራዎች ገና የሚቀሩ መሆናቸው፡፡

የክትትልና ቁጥጥር ሥራውን ለመደገፍ የሚያስችል የጥናት ሥራዎች ቢኖሩም በቂ አለመሆኑንና የየተቋማቱን ዝርዝር ጥናት ያለማካተት ሁኔታና፣ በመስክ ምልከታም ሆነ በአጠቃላይ የክትትል ቁጥጥር ሥራ በሚሠራበት ወቅት በበቂ ባለሙያዎች አባላት እንዲደገፉ ያለመደረጉ ስራዎች ላይ እንቅፋት የፈጠሩ ሲሆን ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የመስክ ምልከታዎች በሚያካሂዱበት ወቅት በጽ/ቤቱ በኩል የሚዘጋጁ ሎጀስቲኮችና አስፈላጊ ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ መቅረብ አለመቻላቸው በመስክ ክትትልና ቁጥጥር ስራው ውስንነት የፈጠረ ተግባር መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.2.3. የዲፕሎማሲ ሥራን አስመልክቶ

**ሀ. በጥንካሬ የታዩ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለያዩ ሃገራት አምባሳደሮችን በማወያየት ለተነሱ ችግሮና የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ ውይይት ለማድረግ ራሱን ችሎ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን የሚሠራ ብቁ አመራር (የሰላምና ውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ) በመመደቡ ምክንያት የመንግሥታችንን እርምጃና መፍትሄ አቅጣጫዎች ለማሳወቅ ሥራዎች መሠራታቸው፡፡ በቋሚ ኮሚቴዎች የሥራ ዘመን ምክር ቤቱ በአህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ መድረኮች ላይ ተገኝቶ መሳተፉና፣ የሌሎች ሀገራት አቻ ተቋማት ተወካዮችን ጋብዞ መቀበሉና ከሀገር ውስጥ ተቋማት ጋርም የምክክር መድረክ አዘጋጅቶ የልምድ ልውውጥ የተካሄደበት ሁኔታ መኖሩ፡፡

**ለ. በእጥረት የታዩ**

የፓርላማ ዲፕሎማስ ሥራ በምክር ቤት ደረጃ በዕቅድ፣ በግልፀኝነት፣ በአሳታፊነትና ተጠያቂነት መርህ አለመመራቱ፣ የምክር ቤቱ ከተለያዩ ሀገሮች አቻ የፓርላማ የወዳጅነት ቡድኖች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ የወዳጅነት ቡድኖች መቋቋማቸው፣ ለወዳጅነት ቡድኑ

ተግባርና ኃላፊነት የተሰጠ መሆኑ እውነት ቢሆንም ለወዳጅነት ቡድኑ ቢሮ የሌለው፣ የሥራ ቀንና ሰዓት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ዕቅድ፣ የአፈፃፀም ሪፖርትና የግምገማ ሥርዓት የሌው መሆኑ፡፡

ምክር ቤቱ ከፓርላማ ህብረት ጋር በሚኖረው ግኑኝነት ላይ የሚሳተፉ አባላት በምክር ቤቱ አመራር የተሰየመ ከሌሎች አገራት ፓርላማ ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት፣ ተግባርና ኃላፊነት መሰጠቱ እውነት ቢሆንም የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በምን ደረጃ እንደተወጡና ምን ችግር እንዳጋጠማቸውና የአገሪቱን ክብርና ጥቅም አስከብሯል ወይስ አላስከበሩም የሚለውን ም/ቤቱን በመወከል በተለያዩ የፓርላማ ህብረትና በዲፕሎማሲ መድረኮች የተሳተፉ ልዑካን ከተልዕኮ በኋላ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የማያቀርቡ መሆኑ፣ በአጠቃላይ የፓርላማ ዲፕሎማሲ የሚለው ሥራ በምክር ቤት ውስጥ በአባላት ዘንድ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ግንዛቤ አለመፈጠሩ፡፡

በመደበኛነት የሚከናወኑ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በዘርፉ ሥራዎችን የሚያከናወኑ ቋሚ ኮሚቴዎችና የምክር ቤት አባላትን በተደራጀ የሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ለማገዝ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች አነስተኛ መሆናቸው፣ የፓርላማ ወዳጅነት ቡድኖች እንቅስቃሴን ደረጃውን በጠበቀ የዕቅድ ክትትል ግምገማና መማማር ስልቶች በመታገዝ ያለመፈጸም፣ በስትራቴጅካዊ ቅኝት ያለማደራጀትና በአብዛኛው እንቅስቃሴያቸው ለፎርማሊቲ ያህል ብቻ መሆኑ፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን በበቂ በጀት አስደግፎ ያለማከናወን፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ከሚያከናውኑ ሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ያለመሥራት እና የፓርላማ ዲፕሎማሲን አስመልክቶ ለምክር ቤት አባላት የሚሰጡ ስልጠናዎችና የአቅም ግንባታ ሥራዎች አነስተኛ መሆን በክፍተትነት ታይቷል፡፡ በሌላ በኩል የተለያዩ አገራዊ ችግሮች ሲከሰቱ በፓርላማ ዲፕሎማሲ አማካኝነት በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት አነስተኛ መሆናቸው በእጥረት የታዩ ዋና ዋና ተግባራቶች ናቸው፡፡

### 4.2.4. የውክልና ሥራን በተመለከተ

#### ሀ. በጥንካሬ የታዩ

በምክር ቤቱ የአሠራርና አባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 በተሻሻለው አንቀጽ 24 መሠረት በዓመት ሁለት ጊዜ አባላት እረፍት ላይ ሲሆኑ በዓመት 2 ጊዜ አባላት ወደ ምርጫ

ክልላቸው እነዲሄዱ መደረጉ። ምክር ቤቱ አባላቱ ወደ ምርጫ ክልላቸው በሚሄዱበት ወቅት አስፈላጊውን የሥራ መነሻ ቼክ-ሊስት ያዘጋጃል፣ ኦረንቴሽን ይሰጣል፣ የትራንስፖርትና የሥራ አበል አመቻችቶ ማሰማራቱ እና ማንኛውም አባል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ከህዝቡ ጋር መገናኘት ይችላል በሚለው መሠረት አልፎ አልፎ ይከናወን የነበረ መሆኑ። በየምርጫ ክልሎቹ ሕዝቡ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች አባላቱ ለፌደራልና ለክልል ተብለው የቀረቡ ጥያቄዎችን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በመለየት ለምክር ቤቱ በማቅረብ ምክር ቤቱ ጥያቄዎቹን በመለየትና በማደራጀት የሚመለከታቸው አስፃሚ መሥሪያ ቤቶች በጥያቄዎቹ ላይ ምላሽ እንዲሰጡ በሸኚ ደብዳቤ የመላክ ሥራ መሠራት መቻሉ።

## ለ. በእጥረት የታዩ

ባለፉት 6 ዓመታት የምክር ቤት አባላት ወደ መራጭ ህዝብ በመሄድ ህዝቡ የሚያነሳቸውን የልማት ጥያቄዎች ይዞ በመምጣትና ለአስፈፃሚ አካላት እንዲላክ ሲደርጉ ቆይተዋል። በምክር ቤቱ በኩል ለአስፈፃሚ መ/ቤቶቹ ለተላኩ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በጊዜ አለመስጠቱና የሚሰጡ ምላሾች ቢኖሩም አጥጋቢ አለመሆናቸው በዚህ ምክንያት አባላት ወደ ምርጫ ክልላቸው ዳግመኛ ለመሄድ እስከ መፍራት መድረሳቸውና ሄደውም ውጤታማ ያለመሆን ችግሮች አጋጥመዋል። ይህም በምክር ቤቱ አባላት ፍላጐት ማነስና መንግሥት አፋጣኝ ምላሽ መስጠት አለመቻሉ ነው።

የምክር ቤቱ አባላት ወደ ምርጫ ክልላቸው ለመሄድ የሚያስችል ትራንስፖርትን በተመለከተ የምክር ቤቱ አባላት ደንቡ ላይ ደረጃውን የመጠነ ትራንስፖርት ይዘጋጅ ቢልም ያለመተግበሩ እና በምክር ቤቱ በኩል የሚከፈለው የትራንስፖርት ገንዘብ ዝቅተኛ መሆኑና አባላት በትራስፖርት ችግር ምክንያት መጉላላት የደረሰባቸው መሆኑና ወደ ምርጫ ክልላቸውም ለመንቀሳቀስ ትራንስፖርት ተግዳሮት መሆኑ ይህም በስራ ላይ እንቅፋት ሲፈጥር መቆየቱ።

ምክር ቤቱ አባላቱ ወደ ምርጫ ክልል ሄደው ሕዝብ እነዲያወያዩ ሲያደረግ ለአባላቱ የሚሰጠው የውሎ አበል ከተሰጣቸው ተግባርና ተልዕኮ አንፃር በቂ አለመሆኑ ከሕዝቡ ጋር የሚደረጉ ውይይቶች አጭርና ጥልቀት የሌላቸው እንዲሁም አጠቃላይ ሕዝቡን ተደራሽ ያደረገ እንዲሆን አለማስቻሉ እና ከወቅቱ የዋጋ ንብረት ጋር ተመጣጥኖ አለመሰጠቱ እንደ ችግር መነሳቱ። በመንግሥት ተቋማት ላይ የሚስተዋሉ የቅንጅት ችግሮች ማለትም የፌደራልና የክልል

ተወካዮች ወደ ምርጫ ጣቢያቸው ሲሄዱ አንድ ላይ ያለመሆንና በምክር ቤቱ ደረጃ የሥራው ባለቤት ያለመሆን ችግር መኖሩን መረዳት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና ምክረ ሐሳቦች/Conclusions and Recommendations/

### 5.1. ማጠቃለያ/ Conclusions/

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሕግ የማውጣት፣ አስፈፃሚ አካላትን መከታተልና መቆጣጠር፣ የመራጮች ውክልና እና የዲፕሎማሲ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ እነዚህን ሥራዎችን ለማከናወን ያስችላቸው ዘንድ ቋሚ ኮሚቴዎች የተለያዩ መከታተያ ቼክ ሊስቶችን በማዘጋጀት በሕግ ማውጣት፣ በክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የውክልና ሥራዎችን ሲያከናውኑ በነበረበት ወቅት የታዩ ክፍተቶች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጋራ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ጠንካራና ደካማ አፈፃፀሞችን በመለየትና በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለይቶ በማሳየት ለተቋሙ በቃልና በፅሁፍ ግብረ- መልስ ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡

በዚህ ጥናት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና አባላት ከላይ በህግ የተሰጧቸውን ስራዎች በሚያከናውኑበት ወቅት በሂደቱ የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፤ ደካማ ጎኖች እንዲሁም ለቀጣይ ፓርላማ እንደ ግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችለውን መልካም ተሞክሮ ለማየት ተችሏል፡፡

#### 5.1.1. ሕግ አወጣጥን በተመለከተ

- የሕግ ማውጣትና ማሻሻልን በተመለከተ የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት ከሚኒስትሮች ምክር ቤት የተመሩላቸውን ረቂቅ ዓዋጆች በጥልቀት በግል እንዲሁም በጋራ በማየት በቋሚ ኮሚቴ ደረጃ ከተወያዩና መግባባት ላይ ከደረሱ በኋላ የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ወደ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በመላክ ሁሉም የቋሚ ኮሚቴ አባላቶቸ ባሉበት በአንድ ድምፅ በማፅደቅ ተቋሙ ወደ ትግበራ እንዲገባ እየተደረገ በነበረበት ሂደት ውስጥ ከተቋሙ እንዲሁም ከሌሎች ሁኔታዎች አኳያ የነበሩ እጥረቶች የነበሩ ሲሆን አባላት ይህንን ለማቻቻልና

የተሻለ አካሄድ ለመፍጥር የተኬደው ርቀት ትንሽ ግምት የሚሰጠው ባለመሆኑ የሚበረታታ ተግባር ነው፡፡

## 5.1.2. ክትትልና ቁጥጥር ተግባርን አስመልክቶ

- የቋሚ ኮሚቴ አባላት የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችን ዕቅድ እንዲሁም የአፈፃፀም ሪፖርት በሚገመግሙበት ወቅት የተለያዩ ጥንካሬዎችንና እጥረቶችን በዚህ ጥናት ለማየት የተቻለ ሲሆን በተቋማቱ በኩል በዕቅድ እንዲሁም በእቅድ አፈፃፀም ዙሪያ ከዛም አልፎ መሬት ላይ የወረደ ተግባር መኖሩን ለማረጋገጥ ወደ ክልሎች በመሄድ የመስክ ምልከታን በማካሄድ የታዩ ግኝቶችን ቋሚ ኮሚቴዎቹ በተቻለ መጠን ለመዳሰስና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር ለአስፈፃሚ ተቋማቱ ግብረ መልስ በመስጠት ለቀጣይ የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው እና በመንግሥት ደረጃ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ተግባራትን ሲፈፅሙ ቆይተዋል፡፡

## 5.1.3. የህዝብ ውክልና ሥራን በሚመለከት

- አባላት ወደ መረጣቸው ሕዝብ በዓመት 2 ጊዜ በመሄድ በህዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎችንና ሀሳቦችን በመያዝ ለሚመለከተው አካል አቀናጅቶ በማቅረብ የህዝቡ ጥያቄዎች እንዲመለሱ ከማድረግ አኳያ ውስንነቶች በተለያዩ ምክንያቶች ቢፈጠሩም እነዚህን እንቅፋቶች ተቋቁሙ ህዝቡ ከመንግሥት የሚፈልገውን ምላሽ ለማሰጠት የሄዱበት አግባብ መልካም የሚባል ተግባር ነው፡፡

## 5.1.4. የዲፕሎማሲን ሥራን በተመለከተ

- የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የትኩረት መስኮች ዙሪያ ተሳትፎዎችን አድርገዋል፡፡ በዚህ መሠረት የወዳጅ ሀገራትና አቻ ፓርላማዎችን የትብብር አድማስ ለማስፋት የሚያስችል እና የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችና ሀገራት መሪዎችና ተጠሪዎቻቸው በምክር ቤታቱ በመገኘት ያደረጓቸዉን ጉብኝቶች፣ ሰላምንና ዴሞክራሲን መሠረት ያደረጉ ትብብሮች፣ በሀገሪቱ ውስጥ እየተካሄዱ የሚገኙ ለውጦችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ዓውድ እንዲኖር

ለማስቻል የግንኙነት ሥራዎች የተለያዩ እንቅፋቶችና ክፍተቶች ባሉበት ሁኔታ የተሠሩ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም የቋሚ ኮሚቴዎች አባላት በሕግ የተሰጧቸውን ተግባራት ለማሳካት የተቻላቸውን ሁሉ በማድረግ በሥራው ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታ የተለያዩ ስልቶችን በመቀየስ እና በጋራ ከሌሎች አባላት ጋር በመወያየትና በመፍታት ሥራዎችን በኃላፊነት ሲተገብሩ የቆዩ ሲሆን በዚህ የሥራ ዘመን ለቀጣይ ፓርላማ ተሞክሮ ሲሆን የሚችል ተግባርም በመፈፀም የሥራ ዘመናቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመፈፀም ችለዋል፡፡

## 5.2. ምክረ ሐሳቦች / Recommendations/

### 5.2.1. በቀጣይ ጊዜ የነበሩ ችግሮችን ለማስወገድ ምክር ቤቱ ሊሠራቸው የሚገቡ ጉዳዮች

- የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስለፓርላማ ከኢፌዴሪ ህገ-መንግሥት ጀምሮ የተለያዩ ህጎች ምን ይላሉ የሚለውን ለይቶ የማወቅ ሥራ የም/ቤቱ አመራርና አባላት ዋና ሥራ መሆን ቢቻል፣

- በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለተግባራዊ አፈፃፀም ሊረዳ የሚችል የ5 ዓመትና የዓመታዊ መደበኛ ዕቅድ ማዘጋጀት የም/ቤቱን አባላት በሙሉ በማወያየት አስፀድቆ ወደ ተግባር መግባት ቢቻል፣

- ም/ቤቱ የህዝብ እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ዋና ማዕከል የሆነ ተቋም እንደ መሆኑ መጠን የግልፀኝነት፣ የፍትሐዊነት፣ የእኩል አሳታፊነትና የተጠያቂነት መርህን ተከትሎ ለምክር ቤቱ በህገ-መንግስት የተሰጠውን ህግ የማውጣት (አዳዲስ ህጎችን ማውጣት፣ ነባር ህጎችን ማሻሻል፣ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ማስፀደቅ እና ውሳኔዎችን ማስተላለፍ)፣ አስፈፃሚ አካላትን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ በምርጫ ክልል ሥራ መፈፀም (ከመራጭ ህዝብ ጋር በዓመት 4 ጊዜ ውይይት) ማድረግ፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ቢቻል፣

- ምክር ቤቱ ዓመታዊ ዕቅዶች እና የዕቅድ አፈፃፀሞች ላይ በየጊዜው አመራሮች እና አባላትና የሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ባለድርሻ አካላት ጋር አጠቃላይ የምክር ቤቱን ሁኔታና የሥራ

አፈፃፀም በጋራ በመገምገም የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን አመራሮች፣ አባላትና ቋሚ ኮሚቴዎች ማበረታታት እንዲሁም ችግሮችን ማረም ተጠያቂነትን ማረጋገጥና የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ መምራት ቢቻል፣ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች ተቋማትን የመመዘን ሥራ ለመሥራት የሚያስችሉ የመመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት የሚከታተሏቸውን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች አፈፃፀሞቻቸውን በየዓመቱ መጨረሻ የመመዘን ሥራ ቢሠራና በተገኘው ውጤት መሠረት አፈፃፀማቸው የተሻለ የሆኑትን የማበረታታት እና አፈፃፀማቸው ዝቅተኛ የሆኑትን የእርምት አቅጣጫ መሥጠት ቢቻል፣

- በዋና ዋና ተግባራት ላይ ትኩረት በማድረግ ሥራዎች በተገቢው የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ የመራጭ ብሎም የኢትዮጵያ ህዝብ ግልፅ፣ ተዓማንነትን ያተረፈ፣ ለህዝብ ጥያቄ ወቅታዊ ትክክለኛና ፍትሐዊ ምላሽ የሚሰጥ፣ ከራሱ ይልቅ የአገርንና የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም፣ አገራዊ አስተሳሰብ ያለው፣ ከመጠቃቃትና መጠቃቀም ተግባር ነፃ የሆነ፣ተመራጮችን እኩል የሚያገለግል፣ ሙስናንና አድሏዊ አሠራርን የማይፈጽምና የሚታገል ሙሉ የህዝብና የአገር ውግንና ያለው ተቋም መሆኑ የተመሰከረለት እንዲሆን ማድረግ ቢቻል፣

- ለሌላ አካላት ጣልቃ ገብነትን የማያስተናግድ በህግ አስፈፃሚና ተርጓሚ ተግባር ውስጥ ጣልቃ የማይገባ፣ የህዝብን ሥልጣን አለአግባብ የማይጠቀም፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሥራን እንደ ግል መዝናኛና መብት አድርጎ የማይጠቀም፣ የህዝብ አለቅነት ሳይሆን የህዝብ አገልጋይነት ሥነ-ምግባርና መርህን የሚከተል፣ የሚፈፅም እና የሚያስፈፅም ምክር ቤት መሆን ቢቻል፣

- አሁን ላለው ም/ቤት ከተቋማዊ ለውጥ በፊት አፅምሯዊና ሥነ ልቦናዊ ለውጥ እጅግ በጣም ወሳኝ በመሆኑ ይህንን የሚያሻሻል አሠራር ተግባራዊ ቢደረግ፣ የምክር ቤቱን አደረጃጀትን በተመለከተ በሕገ መንግሥቱ ተለይተው የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የመከለስ ሥራ ቢሠራ፣

- ሕጎች በሚወጡ ጊዜ ባለድርሻ አካላትን በበቂ ሁኔታ በማሳተፍ የባለቤትነት ስሜትን ማጎልበት ቢቻል፣የምክር ቤቱን አባላት የሚመጥንና በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን ሥልጣን፣ ተግባና ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችል የደመወዝ ክፍያ፣ ጥቅማጥቅምና

ጥረቱን የጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎትና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን የማሟላት ሥራዎች ቢሠሩ፣

### 5.2.2. **ቋሚ ኮሚቴዎችን አስመልክቶ**

- በቋሚ ኮሚቴዎች አባላት የአቅም ውስንነት እንዳይኖር በስልጠናዎችና የእርስ በርስ የመገነባቢያ መድረኮችን አጠናክሮ መሔድ ያስፈልጋል፣
- አባላት ከስራ ገበታቸው እንዳይቀሩ የግምገማና የቁጥጥር ሥርዓትን በማጠናከርና በስልጠና የሚባክኑ የቋሚ ኮሚቴ ቀናቶች ካሉ በሌላ ጊዜ የማተካካት ስራ መስራት ያስፈልጋል፣
- ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሏቸው መ/ቤቶች ወቅቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ከመ/ቤቶቹ ኃላፊዎች ጋር ተወያይቶ መግባባት ላይ መድረስ፣ ክትትሉንም ማጠናከር፣
- ቋሚ ኮሚቴዎች የሚሰጡትን ግብረ መልስና በክትትልና በቁጥጥር ሥርዓት ውስጥ የሚሰጧቸውን አስተያየቶች የሚከታተሏቸው መ/ቤቶች እንደ ግብአትነት እንዲጠቀሙ ክትትልና፣ ቁጥጥር ማድረግ፣

### **5.2.3. በቀጣይ ጊዜ የነበሩ ችግሮችን ለማስወገድ የም/ቤቱ ጽ/ቤት**

- ለም/ቤቱ ጽ/ቤት በሕግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለይቶ ማወቅ፣ መተንተን፣ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ህጋዊና ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፣ ነፃ፣ ገለልተኛና ህብረ-ብሔራዊ የሰው ኃይል አደረጃጀት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ማሟላት የሚችል ጽ/ቤት እንዲሆን ቢደረግ፣
- በሕጉ መሠረት በየሩብ ዓመቱ ከም/ቤቱ ጽ/ቤት አመራሮች፣ ሠራተኞችና ተገልጋይ ባለድርሻ አካላት ጋር አጠቃላይ የም/ቤቱ ጽ/ቤት ሁኔታና ዕቅድ አፈፃፀም በጋራ መገምገም፣ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን አመራርና ሠራተኞች ማበረታታት፣ ችግሮችን ማረም ተጠያቂነትን ማረጋገጥና የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ በመምራት፣ ድጋፉንና አገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል የሚችል ጽ/ቤት ቢሆን፣

- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት በማንኛውም አሠራሩ ከበጀት አንስቶ እስከ አስፈላጊ ግብዓቶች ድረስ ከአስፈፃሚው ተጽኖ በመላቀቅ የራሱን በጀት ራሱ የሚያዘጋጅበትና በምክር ቤት የሚያፀድቅበት እንዲሁም ግብዓቶችን ለማሟት የሚያስችል ግዢንም በተመለከተ በራሱ የሚያስኬድበት አሰራርን ቢከተል ለሥራው የተሻለ ይሆናል፣

- የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ምክር ቤቱን በአስተዳደራዊና በሙያ አገልግሎቶች ለመደገፍ በሚያስችል አግባብ አደራጃጀት አለመኖሩና ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች ወደ ምክር ቤቱ ለማምጣት የሚያስችል ደረጃዎችና ክፍያዎች በማጥናት ወደ ሥራ ለማስገባት ጥረት ቢደረግ፡፡

- ጠንካራ የአባላትን ጥያቄ ያለ አድሎ ሊመልስ የሚችል የፅ/ቤት አመራር በአዲስ መልኩ ማደራጀት ይገባል፣ ጽ/ቤቱ አሁን ያለው ቁመና የተስተካከለ ባለመሆኑ በአዲስ መልክ በአደረጃጀቱ ዙሪያ በሰው ኃይል ስብጥርና አጠቃቀም ሁኔታ በደንብ ተጠንቶ የምክር ቤቱን ስራ ሊያሳልጥ በሚችል መልኩ እንደገና ሊደራጅ ይገባዋል፡፡

- ሠራተኛውን የቤት ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ያለው ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ የቤት ችግር ያሉባቸው ሠራተኞች ቤት የሚያገኙበት የተለያዩ ጥረቶች ቢደረግ፣

# ዋቢ መፅሀፍት (References)


1. የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት ተግባረ እና ኃላፊነት ውሳኔ ቁጥር 7/2011 ዓ.ም
2. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (2013 ዓ.ም) ቋሚ ኮሚቴዎች ለአስፈጻሚ አካላት በሚሰጧቸው ግብረ መልሶች ላይ የቀረበ የዳሰሳ ጥናት
3. በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ከ2008 - 2013 ዓ.ም). የቋሚ ኮሚቴዎች ዓመታዊ እቅዶች
4. በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ከ2008 - 2013 ዓ.ም). የቋሚ ኮሚቴዎች ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች
5. በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ከ2008 - 2013 ዓ.ም).የቋሚ ኮሚቴዎች የመስክ ምልከታ ግብረ-መልሶች
6. በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ከ2008 - 2013 ዓ.ም). የቋሚ ኮሚቴዎች የመስክ ምልከታ ቼክ ሊስቶች

# የቃል መጠይቅ

1. ምክር ቤቱ በ6 አመት የስራ ቆይታው ስራዎችን ሲያከናውንበት የነበረውን ሂደት ምን ይመስላል?
2. በምክር ቤቱ በ6 አመት በህግ የማውጣት ስራ ላይ የነበሩ ጠንካራ ጎኖችና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምን ይመስላሉ?
3. በምክር ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ሥራን አስመልክቶ በ6 ዐመት ቆይታው የነበሩ ጥንካሬዎችና ያሉ ጋጠሙ ችግሮች እንዴት ይታያሉ?
4. የዲፕሎማሲ ስራዎችን በሚመለከት ምክር ቤቱ ባለፉት 6 የስራ ዓመታት ውስጥ የነበሩ ጥንካሬዎችና ያጋጠሙ እንቅፋቶች ምን ይመስላሉ?
5. የውክልና ስራን በተመለከተ ባለፉት 6 አመታት እንዴት ይተገበሩ እንደነበረና በሂደቱም ያጋጠሙ ችግሮች ምን ምን ናቸው?
6. በምክር ቤቱ በፓርላሜንታዊ ስራዎች ዙሪያ እንደ አጠቃላይ የታዩ ጥንካሬዎች፣ ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም ለቀጣይ የስራ ዘመን እነዚህ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ ምን ቢደረግ ይላሉ?
   - ምክር ቤቱን አስመልክቶ?
   - የምክር ቤት ፅ/ቤቱን አስመልክቶ?
7. በምክር ቤቱ የስራ ቆይታ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን የሚሏቸው ምን ምን ናቸው?